# ዕድገትና ለውጥ በኢትዮጵያ ወይስ በፍጥነት

# ወደ ማዕከለኛው ዘመን ጉዞ!

„*Everything in the world now is so delicate –which is merely another way of saying that nobody seems to have any real understanding of how the economic system works at all or why it works so dangerously –that the policy of all parties seems to be rather to bear the ills we have than to fly to others which we know not of.” Prof.Frederick Soddy, Noble Price winner in Chemistry in the 1930s.* **Wealth, Virtual Wealth and Debt: The Solution of the Economic Paradox.**

*መግቢያ*

አንዳንድ ሰዎች ውሸትን ሲዳግግሙ ወይም በውሸት ስም ሲምሉ ሲገዘቱ የመጨረሻ ላይ ዕወነቱን ተናግረው ሰውን ማሳመን የሚችሉ ይመስላቸዋል። የኢህአዴግ ፣ ወይም የህውሃት አገዛዝ ስልጣን ከያዘ ከዛሬ ሃያ አንድ ዐመት ጀምሮ በአገራችን ታሪክ ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ በልዩ ዐይነት የኢኮኖሚ ፖሊስ አማካይነት የኢትዮጵያን ህዝብ የኑሮውን ሁኔታ እንዳሻሻለለትና ፣ ድህነትም በየጊዜው እየቀነሰ እንደመጣ ሲነግረን ሰንብቷል። ባለፈው ጥቅምት ወር እዚህ በርሊን የሶሻል ዲሞክራቲክ የተራድኦ ድርጅት በጠራው ስብሰባ ላይ “የዓለም አቀፍ የሰላምንና ዕድገት ኢንስቲቱሽን“(International Institute for Peace and Development) ወክለው የተገኙት አቶ ስብሃት ነጋ በስብሰባው ላይ እንደተናገሩት ፣ ህውሃት ስልጣን ሲይዝ ኢትዮጵያን ያገኛት እጅግ ወደ ኋላ የቀረች ወይም የበሰበሰች(Moribund) አገር እንደነበረችና ፣ በሳቸውና በፓርቲያቸው ጥረት የተረጋጋች አገር ልትሆን እንደበቃችና ፣ ዕድገትም እንደታየባት በስብሰባው ላይ ለተገኘነው አብስረውልናል። ይህንን ንግግራቸውን ስንሰማ ሰውየው ከሌላ ፕላኔት የመጡ ወይስ ሌላ አገር ተወልደው ያደጉ ናቸው? ብለን ራሳቸንን መጠየቅ የጀመርን ጥቂት አይደለንም።

ቀደም ብሎ የአገራችንን ኢኮኖሚ ዕድገት በሚመለከት ፣ መንግስትም ሆነ የአገዛዙን አቋም የሚደግፉ ድርጅቶችም ሆነ ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቁ ኢኮኖሚስቶች የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በላፉት አስር ዐመታት እጅግ በፍጥነት ከሚያድጉት ኢኮኖሚዎች ውስጥ አንዱ እንደሆነ ለማሳመን ያልሞከሩት ነገር የለም። ይህ በየጊዜው እየተደጋገመ የሚወጣ ስታትስቲክስ እኛንም ግራ እንዳጋባንና ፣ በመጨረሻም ስለ ኢኮኖሚና ስለ ኢኮኖሚ ዕድገት ያለንን አመለካከት እንዳዘበራረቀብን ይታያል። እስከዛሬም ድረስ ስለ ኢኮኖሚ ቲዎሪ ምንነትም ሆነ ስለ ኢኮኖሚ ዕድገት ያለንን አመለካከት ብንመረምርም የዓለም አቀፍ ኮሙኒቲዩው ግፊትና ፕሮፓጋንዳ ከፍተኛ ስለሆነ ፣ ተቃዋሚ ነኝ ብለን እዚህና እዚያ የምንቀሳቀሰው በድፍረት ወደ ውጭ ወጥተን ይህ ዐይነቱ አባባል በቲዎሪም ሆነ በሳይንስ እየመረመን የነሱን አጉል ቅስቀሳ ልናጋልጥ አልቻልንም። በዚህም ምክንያት በዓለም አቀፍ ድርጅቶችና በኢትዮጵያ መንግስት መሀከል የቁጥር ልዩነት ሲኖር ይህን ነገር እንደ ቁም ነገር ወስደን በሱ ላይ በመረባረብ ፣ ለምን የቁጥር ልዩነት ይኖራል እያልን ራሳችንን ከማስጨነቅ በስተቀር የአገዛዙንም ሆነ የዓለም አቀፍ ድርጅቶችን በሳይንስ የማይደገፍና ፣ ምድር ላይ ከሚታየው የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ሊጣጣም የማይችለውን ፕሮፖጋንዳቸውን ልናጋልጠውና ፣ አማራጭ ልናቀርብ በፍጹም አልቻልንም።

ሰሞኑን ለአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን የገንዘብና የዕድገት ሚኒስትሩ አቶ ሱፊያን አህመድ የሁለት ዐመት ተኩሉን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ውጤት ሲያብራሩ ፣ ከአንዳንድ ሁኔታዎች በስተቀር በአጠቃላይ ሲታይ የኢኮኖሚው ዕድገት አመርቂና ጥሩ ውጤት በማሳየት ላይ እንደሆነ በመዝናናት አብራርተዋል። በሳቸውም አገላለጽ ፣ የተተለመው የኢኮኖሚ ዕድገት 11 በመቶ ሲሆን ፣ ኢኮኖሚው ያስመዘገበው ዕድገት ግን 8.5 በመቶ ብቻ ነው። ወደ ዝርዝር የመስኮች ዕድገት ሲመጣ በሚኒስትሩ አገላለጽ ፣ የኢንዱስትሪው ዘርፍ 17.9 በመቶ ያድጋል ተብሎ ሲጠበቅ ፣ ያደገው ግን 13.6 በመቶ

ብቻ ነው። በእርሻውም መስክ እንደዚሁ የተጠበቀውን ግብ መምታት እንዳልቻለና ፣ 8.5 በመቶ ያድጋል ተብሎ የተጠበቀው 4.5 በመቶ ብቻ እንዳደገ ተናግረዋል። ሚኒስትሩ ለማብራራት እንደሞከሩት ፣ የኢኮኖሚው ዕድገት እንደተጠበቀው ግቡን ባይመታም ፣ በአጠቃላይ ሲታይ ኢኮኖሚው በጸና መሰረት ላይ የቆመ መሆኑን ተናግረዋል። ይሁንና ይህ የጸና መሰረት ምን እንደሚመስል በንዑስ-መስክና ፣ በየመስኮቹ ፣ እንዲሁም ደግሞ በየክፍላተ ሀገራት ያሉትን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችና ፣ በኢኮኖሚ መስኩ ቢያንስ ባለፈው ሁለት ዐመት ተኩል ስንት የስራ መስክ እንደተፈጠረ ያቀረቡት ምንም ሀተታ የለም። በደፈናው ኢኮኖሚው በጸና መሰረት ላይ የቆመ ነው ብለው ደምድመዋል።

ይሁንና እዚያ በዚያው ሰሞኑን ፣ የተባበሩት መንግስታት የዕድገት ፕሮግራም ድርጅት ባወጣው የአገሮች የኑሮ መሻሻል መለኪያ(Human Development Index) መሰረት ኢትዮጵያ ከ187 አገሮች 173ኛውን ስትይዝ ፣ በዓለም አቀፍ የኢኮኖሚክ ፎረም(World Economic Forum) መመዘኛ መሰረት ደግሞ ከ144 አገሮች 121ኛውን ይዛለች ይላል። ከአፍሪካ አገሮች ደግሞ 21ኛውን ደረጃ በመያዝ አገዛዙና ፣ የገንዘብና የልማት ሚኒስትሩ የሚሉትን ፋርሽ አድርገዋል። በፎረሙም መለኪያ መሰረት ከ12 መመዘኛዎች ውስጥ ኢትዮጵያ አንዱንም ያላሟላችና ፣ ማሟላትም እንደማትችል የሆነች አገር ለመሆኗ የአገራችንን ሁኔታ በጥብቅ ለሚከታተል መገንዘቡ ከባድ አይሆንም።

ያም ሆኖ ይህንን የሚኒስተሩን ገለጻ የሰማ ወይም ያነበበ ፣ አንዳንዱ በገለጻው ሊረካ ይችል ይሆናል ፤ ሌላው ደግሞ ኢኮኖሚው በዚህ ዐይነት ፍጥነት ካደገ አሁንም ድህነትና የኑሮ መመሰቃቀል ለምን ይታያሉ? የኢኮኖሚ ዕድገትስ ማለት ምን ማለት ነው? በቁጥር ብቻ የሚገለጽ? ግን ደግሞ የማይታይና የማይዳሰስ? እንዲሁም ደግሞ የህዝብን ኑሮ የማያሻሽልና ይባስ ብሎ የሚያደኽይ? ብሎ መጠየቁ አይቀርም። እስካሁን ድረስ በኛ አገር ምሁራን ብቻ ሳይሆን በብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮች መሀከል ያለው ግራ መጋባት በኢኮኖሚ ዕድገት ፣ በህዝቦች ኑሮ መሻሻልና ፣ እንዲሁም ተሳስሮ አንድን አገር በጸና መሰረት ላይ መገንባትና ፣ ለዚህ ሁሉ መሰረቱ ደግሞ የማያቋርጥ የሳይንስና የቴኮኖሎጂ ፈጠራ መሆኑ ተብራርቶ የተመለሰ አይደለም። በህብረ-ብሄር ፣ በህብረተሰብና በኢኮኖሚ ዕድገት መሀከል ያለው ዲያሌክቲካዊ ግኑኝነት ተብራርቶ እስካልተቀመጠና ፣ ሌላ አማራጭ እንዳለና ለሱ መታገል እንደሚያስፈልግ ቅሰቀሳ እስካልተደረገ ድረስ ፣ የኛ ህዝብም ሆነ ብዙ የሶስተኛው ዓለም አገር ህዝቦች ለብዙ መቶ ዐመታት በጨለማ ዓለም ውስጥ እንደሚኖሩ ከአሁኑ መናገር ይቻላል። በዚህም ምክንያት አገዛዙም ሆነ እሱን የሚደግፈው የዓለም ኮሙኒቲ እየደጋገሙ የሚሉንን ከመቀበል በስተቀር ምንም ፋይዳ ያለው ነገር ልንሰራ አንችልም። በዚህ በኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ያለውን አስቸጋሪ ግንዛቤ ለመረዳት የአንድ አገር ኢኮኖሚ እንዴት እንደሚለካ ጠጋ ብለን እንመልከት።

## ዘመናዊ የኢኮኖሚ ዕድገት መለኪያ ዘዴ !

በመሰረቱ አንድ አገር በዐመት-በየኳርታሉ ወይም በየስድስት ወርም ሊሆን ይችላል- የአመረተችው ጠቅላላ ምርትና የአገልግሎት ክንዋኔ ካለፈው ዐመት ጋር በሞኔቴሪ ወይም በገንዘብና ፣ በጊዜው የገበያ ዋጋ ሲለካ በቁጥር የጨመረ ወይም የቀነስ እንደሆን ኢኮኖሚው አድጓል ወይም ቀንሷል ማለት ይቻላል። ይህንን በፎርሙላ አቀራረብ ስንመለከተው ታች ባለው መልክ ማየት ይቻላል።

$$\frac{GDP_{MP\ t=1}}{GDP_{MP\ t=0}} - 1 > 3\%$$

የላይኛው ፎርሙላ የአንድን አገር አጠቃላይ የምርት ዕድገት ካለፈው ዐመት ጋር ሲወዳደር የሚያሳይ ሲሆን ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ይህ በራሱ በቂ የዕድገት መለኪያ አይደለም። ስለዚህም የህዝቡን የነፍስ ወከፍ ወይም በራስ ሲተመን ገቢ ለማወቅ ከተፈለገ አጠቃላዩ የዕቃ ምርትና የአገልግሎት ክንዋኔ ፣ ለምሳሌ እንደ ባንክና ኢንሹራንስ አገልግሎት ፣ እንደ ጋራዥ ስራዎችና የሆቴል ቤቶችና እንዲሁም የትራንስፖርቴሽን አገልግሎቶች ወዘተ... ተደምረው በአንድ አገር ውስጥ በሚኖር ህዝብ ቁጥር ሲካፈል የነፍስ ወከፍ ገቢን ማግኘት ይቻላል። ይህ አጠቃላዩ የነፍስ ወከፍ ገቢ ግን በየዐመቱ በዋጋዎች ከፍና ዝቅ የሚለውን የገቢ ቅነሳ አያካትትም። ስለዚህም ግሽበትን ስሌት ውስጥ ሳያገባ የሚተመን ነው ማለት። ግሽበትን ስሌት ውስጥ ካስገባን አንድ ሰው በዐመት

በሚያገኘው ገቢ ገበያ ላይ ወጥቶ ምን ያህል የፍጆታ ዕቃዎችን ለመግዛትና ፣ ለቤት ኪራይ ፣ ለመብራት ወይም ለትራንስፖርቴሽንና ለሌሎች የአገልግሎት ነክ ነገሮች መክፈል እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል። በዚህም ምክንያት የአንድ አገር ኢኮኖሚ ዕድገት በገንዘብ ሲተመንና ፣ በዕቃዎች መወደድ የተነሳ የአንድ ሰው የመግዛት ኃይል ከቀነሰ ተጨባጩን ገቢ(Real Income) ማግኘት እንችላለን ማለት ነው። በሌላ ወገን ግን በአንድ አገር ውስጥ የሚመረተው ምርትና አገልግሎት በገንዘብ ተተምኖ በህዝብ ብዛት ሲካፈል እያንዳንዱ ሰው ያንን ያህል ይደርሰዋል ማለት አይደለም። ይህ ትመና በአንድ አገር ውስጥ ሊኖር የሚችልን የገቢ ክፍፍል ልዩነት አያካትትም። በመሆኑም በብዙ አገሮች በሰራተኛውና ሀብትን በሚቆጣጠሩ ፣ ወይም በማኔጀሮችና በሄጅ ፈንድ አስተዳዳሪዎች መሀከል ከፍተኛ የገቢና የሀብት ክፍፍል ልዩነት እንዳለ የሚወጡት ስታትስቲክሶች ያረጋግጣሉ። ከዚህም በሻገር የጂዲፒ አጠቃቀምና አሰላል በየአገሮች መሀከል ያለውን የቴክኖሎጂ ዕድገት ልዩነት ፣ የገበያን ስፋት ፣ አጠቃላዩን ዕድገትና የብሄራዊ ሀብትን(National Wealth) መጠን ልዩነት መለኪያ ሊሆን አይችልም። ለምሳሌ የአንድ የሶስተኛው ዓለም ኢኮኖሚ በ10 በመቶ ቢያድግና ፣ በሌላ ወገን ደግሞ የአንድ የካፒታሊስት አገር ኢኮኖሚ በሶስት በመቶ ቢያድግ ፣ በሶስት በመቶ የሚያድገው የካፒታሊስት ኢኮኖሚ የስራ መስክ ለመክፈትና ተጨማሪ የመግዛት ኃይልን የማሳደግ ኃይሉ በብዙ እጅ ይበልጣል።

ከላይ የቀረበውን ዝርዝር ጉዳይ በይበልጥ ለመረዳት በአንድ አገር ውስጥ ሊኖሩ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ ወይም ያሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን ጠጋ ብለን እንመልከት። ከሞላ ጎደል በየኢኮኖሚ መስኮች መሀከል ያለው ወይም ሊኖር የሚችለው መተሳሰር በከፊል የአንድ አገር ኢኮኖሚ ዕድገት ምን እንደሚመስል ያመለክተናል። እነዚህም እንደሚከተሉት ናቸው ፤

አጠቃላዩ የምርት ክንዋኔ

- ህዝብ ለፍጆታም ሆነ ለአገልግሎት የሚያወጣው ወጪ ፣
- አዳዲስ ኢንዱስትሪዎችን ለመትከልና ምርት ለማምረት የሚውለው መዋዕለ-ነዋይ
- አጠቃላይ የግንባታ ስራ ፣
- ወደ ውጭ የሚላክ ምርትና አገልግሎት(Export)

የእነዚህ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች በየዐመቱ ማደግና መቀነስ እስከተወሰነ ደራጃ ድረስ የአንድን አገር የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ወይም የዕድገት ሁኔታ ያሳዩናል። በሌላ አነጋገር ፣ ለምሳሌ በኢንዱስትሪው መስክ በአንድ ንዑስ-መስክ ብቻ ሳይሆን ፣ በተለያዩ ንዑስ መስኮች ሰፋ ያለና ጠለቅ ያለ የመዋዕለ-ነዋይ እንቅስቃሴ ከተካሄደ ኢንዱስትሪዎች የግዴታ ለስራ ፈላጊው የስራ መስክ ይከፍታሉ። በዚህ መልክ እንደ አጠቃላዩ የኢኮኖሚ ሁኔታና የዕድገት ደረጃ የሰራተኞችም የገቢና የመግዛት ኃይል ይጨምራል። ለምሳሌ በኢንዱስትሪ መስክ ውስጥ ተቀጥሮ የሚሰራው ሰራተኛ በሚያገኘው ገቢ ራሱ የሚያመርተውን ገዝቶ መጠቀም የማይችል ከሆነ ፣ ለፍጆታው በኢንፎርማል መስክ ወይም ከእጅ ወደ አፍ በሚታረሰው የገበሬው የምርት እንቅስቃሴ ላይ የሚመካ ከሆነ ለጠቅላላው የኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋፅዖ ማድረግ አይችልም። በስሌቱ መሰረት በብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮች የፀጉር ስራ ቤቶች ፣ የጠላና የጠጅ መሸጫ ቤቶች ፣ እናጢዎችና የሱቅ በደረቴዎች ወዘተ... በነዚህ መስክ የሚመረቱ ከጠቅላላው ወይም ዘመናዊ ከሚባለው መስክ ከሚመረተው ጋር ስለማይደመሩ ፣ የሰራተኛው ገቢ ለአጠቃላዩ የኢኮኖሚ ዕድገት የሚያበረክተው አስተዋፅዖ በጣም ዝቀተኛ ነው ወይም አልቦ ነው ማለት ይቻላል። በሌላ ወገን ደግሞ ኢንዱስትሪዎች እንቅስቃሴያቸውን ሊያስፋፉና ምርታቸውን ሊጨምሩ የሚችሉት የህዝቡ የመግዛት ኃይል በየጊዜው እያደገ ከሄደ ብቻ ነው። ይህ ሁኔታ በሌለበት ኢኮኖሚ ውስጥ ኢንዱስትሪዎች የግዴታ የምርት ክንዋኔያቸውን እንዲቀንሱ ይገደዳሉ። ይህ በራሱ ደግሞ አሰሪዎቹ በጥቂት የሰው ጉልበት ብቻ የምርት ክንዋኔያቸውን እንዲያካሂዱ ይገደዳሉ ማለት ነው። ለምሳሌ በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ መጀመሪያ ላይ የምትክ ኢንዱስትሪ ተከላ(Importsubstitution Industrialzation) ሲካሄድ ብዙዎች ኢንዱስትሪዎች ከረዥም ጊዜ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገትና ህብረተሰብአዊ የሀብት ክምችት አንፃር ታቅደው የተተከሉ ባለመሆናቸው በዚህ መስክ የሚመረተውን ምርት ገዝቶ ይጠቀም የነበረው በጣም ጥቂቱ የህብረተሰብ ክፍል ብቻ ነበር። በመሆኑም በእዚህ ዐይነቱ የኢንዱስትሪ መስክ ተቀጥሮ ይሰራ የነበረው በቂ ደሞዝ ስለማይከፈለው በደሞዙ ገዝቶ ራሱንና ቤተሰቦቹን ያስተዳድር ይነበረው ኢንፎርማል ሴክተር ከሚባለው መስክ እየገዛ ነበር። በዚህም ምክንያት ይህ ዘመናዊ እየተባለ ይጠራ የነበረው መስክ በዝቅተኛ የማምረት ኃይል ብቻ ያመርት ነበር። ከዚህ ስንነሳ በዚህ መልክ የተቀናጀውን የኢንዱስትሪ ተከላ አሉታዊ ውጤት መገንዘቡ ከባድ አይሆንም።

ይህ ከላይ የተዘረዘረው ብቻ የአንድን አገር የኢኮኖሚ ዕድገት ደረጃና አጠቃላዩን እንቅስቃሴ ሊያሳየን በፍጹም አይችልም። በመጀመሪያ ደረጃ በመዋዕለ-ነዋይ እንቅስቃሴ የተለያዩ ደረጃዎች አሉ። እንደ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ስፋትና ጥልቀት የመጀመሪያው መዋዕለ-ነዋይ ፣ የማስፋፊያ መዋዕለ-ነዋይና ፣ ገበያ በውድድር የሚሰራ ከሆነ የኢንዱስትሪ ባለቤቶች የማምረቻን ዋጋ ለመቀነስ ሲሉ የጥሬ-ሀብትን አጠቃቀም ለመቀነስና በተወሰነ ሰራተኛ ብቻ ብዙ ለማምረት የሚያስችላቸውን ፣(Productivity) ዘመናዊ ኢንዱስትሪዎችን(Rationalization Investment or Capital deepening) ይተክላሉ ማለት ነው። ይህ ዐይነቱ የመዋዕለ-ነዋይ ክንውን በብዙ ኢንዱስትሪ አገሮች በተለይም ከ1970ዎቹ መጀምሪያ ላይ ጀምሮ የሚሰራበት የውድድርና የማምረቻ ዋጋ መቀነሻ ዘዴ ነው። ለእንደዚህ ዐይነቱ እንቅስቃሴ ደግሞ የግዴታ በየጊዜው ሳይንስና ምርምር መካሄድ ሲኖርበት ፣ በጥራትና በፍጥነት እንዲሁም በአጠቃላይ ሲታይ የምርትን ዋጋ ሊቀንሱ የሚችሉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ይመረታሉ ፣ ይተከላሉም ማለት ነው። ይህ ከላይ የተዘረዘረው ለአጠቃላዩ የኢኮኖሚ ዕድገት ተጨማሪ የመለኪያ ዘዴ ሲሆን ፣ እንደገና ይህ በራሱ በቂ ስዕል ሊሰጠን አይችልም።

የጠቅላላውን የኢኮኖሚ ዕድገት ትርጉም ለመረዳት በየኢኮኖሚ መስኩና ፣ በተለያዩ መስኮች መሀከል ያለውን የንግድ ልውውጥ ወይም መተሳሰር (Linkages) ጠጋ ብሎ መመልከት ያስፈልጋል። ይህ ደግሞ የአንድ አገር ኢኮኖሚ የቱን ያህል በስራ-ክፍፍል የዳበረና ሰፋ ያለ ገበያ ይኖረው አይኖረው እንደሆን ያሳየናል። ይህንን መረዳት ስንችልና ፣ እንደዚህ ዐይነቱ የኢኮኖሚ መተሳሰር ሲኖር ምርት በየጊዜው በጥራትም ሆነ በብዛት ማምረት ይቻላል። በዚህ መልክ ደግሞ አንድ አገር ብሄራዊ ሀብት መፍጠር መቻሏንና አለመቻሏን መገንዘብ እንችላለን። ይህም ማለት የአንድ አገር የምርት ክንዋኔ በየደረጃዎች በአንድ አገር ውስጥ የሚካሄድ ከሆነና ፣ አንደኛው ንዑስ-መስክ ለሌላው እንደ ገበያ የሚያገለግል ከሆነ ፣(Value-added chain effect) በእርግጥም አጠቃላይ የሆነ የሀብት ክምችት(General Capital Accumulation) መፍጠር ይቻላል ማለት ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ ሌሎችን ነገሮች በማካተት ስለአንድ አገር ሰፊ ገበያ ወይም የተወሳሰበ የምርትና የንግድ እንቅስቃሴ ማውራት እንችላለን።

እንደሚታወቀው ማንኛውም አገር ምርት ማምረቻና መነገጂያ ወይም መገበያያ ብቻ ሆኖ መታየት የለበትም። አብዛኛውን ጊዜ በኢኮኖሚ ዕድገት ስሌት ውስጥ የማይገቡ የቦታና የጊዜ(Space and Time)ጉዳዮች አሉ። እንደሚታወቀው ስለ ኢኮኖሚ ዕድገት ወይም ምርት በቁጥር መጨመር ስናወራ ፣ ማንኛውም የምርት ክንውን በአየር ላይ የሚካሄድ ሳይሆን በምድር ላይ ነው። ይህ ማለት ኢንዱስትሪዎች የሚተከሉበትና የሚያመርቱበት ቦታና ዕቃዎቻቸውን በነጋዴዎች አማካይነት የሚሸጡበት መገበያያ ቦታ እንዲኖር ያስፈልጋል። ይህ ደግሞ ጉልት ሳይሆን በደንብ የተዋቀረና ግልጽ የሆነ ፣ እንዲሁም የሰውን ልጅ የሚስብ የመገበያያ ቦታ መሆን አለበት። በሌላ አነጋገር ስለ ኢኮኖሚ ዕድገት በምናወራበት ጊዜ ስለከተማዎችና ስለመንደሮች አቀራረጽና አገነባብ ፣ እንዲሁም ደግሞ ጥበባዊ ሆነው እንደ አስፈላጊነታቸው ስለመገንባታቸውና ስለመደራጀታቸው ሁኔታ በደንብ መገንዘብ ይኖርብናል። እንደሚታወቀው አንድ አገር ህዝብ በዘፈቀደ የሚኖርባት ሳትሆን ከተማዎችም ሆነ መንደሮች ፣ ለትናንሽና ለማዕከለኛ ኢንዱስትሪ የሚያገለግሉ ቦታዎች ፣ ለመኖሪያ ቦታዎችና ለመገበያያ የሚሆኑ ፣ ለትምህርትና ልዩ ልዩ አገልግሎት መስጫ ቦታዎች ፣ የህክምና አገልግሎት ፣ በአጠቃላይ የመጫወቻ ቦታዎች ፣ ለህጻናትም ሆነ ለትላልቅ ሰዎች ፣ የመዝናኛ ጋርደኖችና መናፈሻዎች ፣ የመንግስት መስሪያ ቤቶችና ልዩ ልዩ የምርምር ኢንስቲቱሽኖች ፣ የሲቭል ሶሳይቲ መስሪያ ቤቶች ፣ ቡና ቤቶችና የምግብ ቤቶች ፣ ሙዚየሞችና የቲያትር አዳራሾች ፣ ልዩ ልዩ ዝግጅቶች የሚካሄድባቸው የመሰብሰቢያ አዳራሾች ፣ እንዲሁም መጠነኛና ትላልቅ ሆቴል ቤቶች ወዘተ...በገበያ ኢኮኖሚ አወቃቀርና ክንውን እንዲሁም በኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ይኖራቸዋል። በተጨማሪም አደጋ በሚከሰትበት ጊዜ በፍጥነት ሊደርሱ የሚችሉ እንደ እሳት አደጋ መኪናዎች ፣ ፈጣን የህክምና አገልግሎት ሰጪ መኪናዎች ወዘተ...በስሌት ውስጥ መግባት አለባቸው። እንደዚህ ዐይነቱ የከተማ አወቃቀር በሌለበት ቦታ ስለ ኢኮኖሚ ዕድገት ማውራት አይቻልም። ወይም ስለ ኢኮኖሚ ዕድገት በሚወራበት ጊዜ ዝም ብሎ በጂዲፒ ብቻ የሚሰላ የሚመስል ከሆነ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ህዝቦች ግራ ተጋብተው በውዥንብር ዓለም ውስጥ እንዲኖሩ ይደረጋል። በዚህም መልክ ይህ በእግዚአብሄር አምሳል የተፈጠረ የሰው ልጅ የገበያ ኢኮኖሚ በሚለው ብቻ ስለሚጠመድ የመፍጠር ችሎታው መታፈኑ ብቻ ሳይሆን ፣ ስነ-ስርዓት ያለው ኑሮ እንዳይመሰርት ይታገዳል። በተለይም በዚህች ዓለም በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ አፈጮሊዎች ተንቀሳቃሽ ቴሌፎናቸውን ኪሳቸው ውስጥ ወይም ጆሮአቸው ላይ ማዳመጫ ሰክተው ግራ ተጋብተው ሌላውን ግራ የሚያጋቡ እዚህና እዚያ ሲፖፖጡ ስናይ በእርግጥም እነዚህ ዘመን-የወለዳቸው የሚነግሩን የገበያ

ኢኮኖሚ ትክክል ነው ብለን አምነን እንቀበል ይሆናል። እንደነሱም ለመሆን እንመኝ ይሆናል። ይህ ዐይነቱ ከውነተኛ ስልጣኔ ጋር ያልተያያዘ የአኗኗር ስልትና የፍጆታ አጠቃቀም የብዙ ሶስተኛው ዓለም አገር ወጣቶችን ዝንባሌያቸውን እያበላሸና ለስራ ያላቸውን ፍላጎት እያኮላሸው ለመሆኑ ሁኔታዎችን ለሚከታተል ሊገነዘብ ይችላል። እንደምናየው እንደዚህ ዐይነቱ በተለይም በንግድ ላይ የተመረኮዘ የገበያ ኢኮኖሚ አስተሳሰብ ከብራዚል እስከ ሚክሲኮና ፣ እስከናይጄሪያና ኢትዮጵያ የመሳሰሉትን አገሮች በማዳረስ ሀብቶቻቸውን ወግ ባለውና በተቆጠበ መልክ እንዳይጠቀሙና ጥበባዊ የሆነ ስርዓት እንዳይገነቡ አድርጓቸዋል ፤ እያገዳቸውም ነው።

ስለ ኢኮኖሚ ዕድገት በሚወራበት ወቅት በአንድ ቦታ ብቻ የሚካሄድ አይደለም። የኢኮኖሚ ዕድገት ትርጉም የሚኖረው በአንድ አገር ውስጥ ሰፋ ባለ መልክ ሲካሄድ ፣ የምርት ክንውን በየክፍለ-ሀገሮች ፣ ወረዳዎችና ምክትል-ወረዳዎች ፣ እንዲሁም በትናንሽ መንደሮች ሁሉ እንደ የጥሬ-ሀብት ግኝት ሁኔታ ሲመረት በዕርግጥም ስለገበያ ኢኮኖሚና ስለ ኢኮኖሚ ዕድገት ማውራት እንችላለን። ይሁንና ደግሞ ሰፋ ያለ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ሊኖር የሚችለው የመመላለሻ መንገዶች ፣ ለምሳሌ እንደ ጥሩ ጠባብና ሰፋ ያሉ የመኪና መንገዶች ፣ የባቡር መገናኛ ሃዲዶችና የአውሮፕላን ማመለሻዎች ፣ በአገር ውስጥ ለመርከብ መሄጃ የሚያገለግሉ ባህሮች ወዘተ... ካሉና በየጊዜው የሚስፋፉ ከሆነ ስለ ኢኮኖሚ ዕድገት የተሟላ ስዕል ይሰጡናል። በተቀላጠፈ የመገናኛ ሁኔታ ብቻ ነው ሰዎችንና ዕቃዎችን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ማመላለስ የሚቻለው። በተለይም ራሱ ጊዜ በኢኮኖሚ ክንዋኔ ስሌት ውስጥ ወሳኝ ሚናን በሚጫወትበት ዓለም ውስጥ ከላይ የተዘረዘሩትን የማያሟላ አገር ስለ ገበያ ኢኮኖሚና ስለ ኢኮኖሚ ዕድገት ሊያወራ በፍጹም አይችልም። ከዚህ ስንነሳ የጊዜ ኢኮኖሚ የሚለው ከስፔስ ጋር ተደምሮ በኢኮኖሚ ዕድገት አሰላል ውስጥ ከፍተኛ ሚናን ይጫወታል ማለት ነው።

ይህ ብቻ አይደለም ፤ ከማርክስ ጀምሮ እስከ ሹምፔተር ድረስ ያሉ ታላላቅ የኢኮኖሚና የህብረተሰብ ሳይንስ ተመራማሪዎች እንደሚያስተምሩን ፣ ካፒታሊዝም ካለባንክና ሰፋ ብሎ ካልተደራጀ የፊናንስ ገበያ ሊንቀሳቀስና ፣ በየጊዜው አዳዲስ የፈጠራ ስራዎችን ማካሄድ እንደማይቻልና ፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እስካልተቋቋሙ ደግሞ ሰፋ ያለ የገበያ ወይም የካፒታሊስት ኢኮኖሚ መዳበር እንደማችይል ነው። በዚህም መሰረት ብድር(Credit) ለካፒታሊዝም ዕድገት ዋና አንቀሳቃሽ ኃይል ነው። በካፒታሊዝም ዕድገት ውስጥ ባንኮች በኢንዱስትሪዎች ላይ ያላቸውን ሚና ዝቅ አድርጎ መመልከት አሉታዊ ተፅዕኖ መኖሩ ብቻ ሳይሆን ፣ በተለይም በአጠቃላይ ሲታይ የገንዘብን ባህርይ ማደግና ህብረተሰብአዊ ኃይል ሆኖ መውጣት እንዳንገነዘብ ያደርገናል። ስለሆነም በተለይም በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ ገንዘብ በፍጥነት መሽከርከርና(Velocity of Money) እንዲሁም ልዩ ልዩ ገጽታዎችን መውሰድ ከዚህ ዐይነቱ በጥልቀትና በስፋት ከሚካሄድና ከሚያድግ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ የተነሳ ነው። በብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮች ግን ገንዘብ ዝግ ብሎ መሽከርከሩ ብቻ ሳይሆን ወደ መዋዕለ-ነዋይ ወይም ካፒታል ለመለወጥና ህብረተሰቡን ለማዳረስ ያለው አቅም በጣም ደካማ ነው። በሌላ ወገን ደግሞ በካፒታልሲት አገሮች ውስጥ ባለፉት ሰላሳ ዐመታት የፊናንስ ካፒታል ከዕውነተኛና ጥንታዊ ባህርይው እየተላቀቀ በመምጣቱና ፣ ለኢንዱስትሪዎች ብድር ከማቅረብ ይልቅ የአየር በአየር ንግድ (Speculation) ውስጥ በመሳተፍ በተጨባጩ የኢኮኖሚ ዘርፍና በፊናንስ ካፒታል መሀከል ከፍተኛ ክፍተት በመታየቱ የገንዘብ ሚና ግራ እያጋባ መጥቷል። በዓለም ገበያ ላይ በተለያየ መልክ የአየር በአየር ንግድ በመጧጧፉ ምክንያት በተለያየ መልክ የሚሽከረከረው የገንዘብ መጠን በብዙ እጥፍ እንደሚበልጥ ይታወቃል። ይህም ማለት ገንዘብ ለገንዘብ ተብሎ ትርፍ የሚካበትበት ሆኖ በመውጣት ባንኮችና የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ሳይቀሩ ወደ ማጭበርበር ተግባርነት ተሰማርተዋል። ለጡረታዬ ይሆነኛል ብሎ ያሰበውን ሰራተኛና ሽማግሌ ገንዘቡ በመሰብሰብና በቁማር መልክ በመጫወት አብዛኛውን ህዝብ መቀመቅ ውስጥ ከተውታል። ይህም ማለት ምን ማለት ነው? ስለካፒታሊዝም በምናወራበት ጊዜ በተወሳሰበ መልኩ መረዳትና አሉታዊ ጎኑንም ማጤንና መገንዘቡ በተለይም በፖለቲካ ውስጥ እንሳተፋለን የሚሉ ቀደም ብለው ጥንቃቄ እንዲወስዱ ያስችላቸዋል።

ስለ ኢኮኖሚ ዕድገት(Economic Growth and Economic Development) በሚወራበት ጊዜ ፣ የሚወራውን ወይም በፕሮፓጋንዳ መልክ የሚቀርበውን ለመረዳት በየጊዜው ጠጋ ብሎ መመርመሩ ነገሩን የተሻለ ግልጽ ያደርገዋል። በተለይም የማቲማቲካል ሞዴሎች በኢኮኖሚክስ ስሌት ውስጥ ከፈተኛ ሚና በሚጫወቱበት ዓለም እሱን የሚያይ ቶሎ ብሎ ሊደናገር ይችላል። እንደሚታወቀው በጣም የተወሳሰቡ ነገሮችን በማቲማቲክስ ማጠናቀር አይቻለም። በተለይም እንደ ጂዲፒ የመሰሳሉት የዕድገት መለኪያዎች በቀጥታ

የሂሳብ ስሌት(Linear Mathematic) ስለሚሰሉ የተወሳሰበውን የኢኮኖሚክስ ዓለምና ተለዋዋጩን የሰው ባህርይና የፍጆታ አጠቃቀም አስልቶ ማቀረብ በፍጹም አይቻልም። ይህንን ግልጽ ለማድረግ ፣ ለምሳሌ አንድ አገር በዓመት ውስጥ የተለያዩ ምርቶችን ታመርታለች። እነዚህን ምርቶች ለማምረት እንደ ሰራተኛ ፣ የተለያዩ ማሽኖች ወይም በአጠቃላይ ካፒታል ፣ የጥሬ-ሀብትና በየጊዜው አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የሚፈጥሩና ፣ የተፈጠሩትን ቴክኖሎጂዎች ተግባራዊ የሚያደርጉ ትጠቀማለች። እነዚህ ነገሮች አንድ ላይ በመጣመር የሚያመርቱት ምርት በአጠቃላይ በገንዘብ ሲተመን አንድ አገር ይህን ያህል ምርት አምርታለች ማለት ይቻላል። ይሁንና ግን የአንድ አገር ጠቅላላ ዐመታዊ ምርት በቲኮኖሎጂዎች መቀያየር ከፍና ዝቅ ሊል ይችላል። የኢኮኖሚ ዕድገትንም ከፍና ዝቅ እንዲል የሚያደረጉት ሌሎች ነገሮችም አሉ። እነሱን እንተውና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች በሚፈጠሩበት ጊዜ ካፒታሊስቶች የተሻለ ለማምረት ሲሉ አዳዲስ ማሽኖችን ይተክላሉ። በተጨማሪም አዳዲሱን ማሽኖች የሚቆጣጠር ሰራቶች ይቀጥራሉ ፤ ወይም ደግሞ እዚያው ተቀጥረው የሚሰርቱን ሰራተኞች ለተወሰነ ጊዜ ስልጠና እንዲያገኙ ያደርጋሉ። ይህም ማለት አዳዲስ የሚፈጠረው ቴክኖሎጂና ተጨማሪ ዕውቀት የግዴታ ለኢኮኖሚው ዕድገት ወሳኝ ሚናን ይጫወታሉ። እነዚህ ነገሮችና ሌሎችም ተደምረው ስለጂዲፒ ሊኖረን የሚችለውን ግንዛቤ በየጊዜው እንድንገመግምና በጥርጣሬ እንድንመለከተው ይረዱናል። ይህ ብቻ ሳይሆን ይህ ዐይነቱ የማቲማቲክ አሰላልና የኢኮኖሚ ዕድገት አስተሳሰብ ስለ ዕውነተኛ የሰው ልጅ ስልጣኔ የሚያወራው ምንም ነገር የለውም። ይህን ሁሉ አስቸጋሪ ሁኔታ ትተን የአገራችንን ኢኮኖሚ ዕድገት ለመረዳት ከላይ ቀደም ብዬ ከዘረዘርኩት የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ዕድገት መመሳል ጋር ሊኖር የሚችለውን ልዩነት ጠጋ ብለን እንመልከት።

ለምሳሌ የኢህአዴግ መንግስት በአለፉት አስር ዐመታት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በአማካይ ሲታይ 10 በመቶ እንዳደገ ሲነግረን ከርሟል። ይህንንም እነ ዓለም የገንዘብ ድርጅትና በጠቅላላው የዓለም ኮሙኒቲው ያረጋግጣሉ። ይሁንና ግን በኢኮኖሚ ዕድገት ታሪክ ውስጥ ስንትና ስንት የፈጠራ ስራዎች በተካሄደባቸው የካፒታሊስት አገሮች ውስጥ እንደ ኢትዮጵያ ዐይነቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ታይቶ አይታወቅም። ለምሳሌ ፕሮፌሰር ሁንትና ፕሮፌሰር ሼርማን የሚባሉት ሁለት የአሜሪካ ፕሮፌሰሮች ፣ Economy from a Traditional and Radical Point of View፣ በሚለው መጽሀፋቸው ውስጥ የአሜሪካን ኮንግረስ ያቀረበውን ሀተታ እንደዚህ ብለው ይመዘግባሉ። „ከ1839-1879 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የአሜሪካን ኢኮኖሚ በግምት በተጨባጭ 4,3% ፣ ከ1879-1919 ዓ.ም ደግሞ በ3,7% ፣ ከ1919-1959 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ደግሞ 3% እንዳደገ ይገልጻሉ። ለዚህ ዕድገት የአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ግኝት ወይም ፈጠራ 50% አስተዋፅዖ እንዳበረከተ ይናገራሉ።

ከዚህ ስንነሳ ምንም ዐይነት የቴክኖሎጂ መሰረት የሌላትና ፣ እንዲሁም የሳይንስና የቴክኖሎጂ የምርምር ጣቢያ የሌለት እንደ ኢትዮጵያ የመሰለች አገር ይህንን ዐይነቱን በየጊዜው በአገዛዙ የሚደሰኮረውን የኢኮኖሚ ዕድገት እንዴት ልታስመዘግብ ትችላለች? ይህ ብቻ ሳይሆን ፣ ለአንድ አገር ዕድገት የጀርባ አጥንት ሆኖ ሊያገለግል የሚችል የማሽን ኢንዱስትሪና ፣ ይህንንን ዲዛይን የሚያደርግ የኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ፣ በተጨማሪም የኤሌክትሪካልና የኤሌክትሮኒክስ ኢንዱስትሪ የሌላት አገር ይህን ያህል የኢኮኖሚ ዕድገት እንዴት ልታስቆጥር ቻለች? ለምሳሌ የዓለም ባንክ በ2006 ዓ.ም ባወጣው ዘገባና ፣ በ2010 ዓ.ም በጀርመን የቴክኒካል ተራድዖ ድርጅት ውስጥ በቀረበው ሀተታ መሰረት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ለዕድገት የሚሆኑ መሰረቶች ወይም ቅድመ-ሁኔታዎች እንደሚጎሉት ያብራራል። በጥናቱም መሰረት ፣ የኬሚካል ፕሮሴሲንግ ኢንዱስትሪ ፣ የኤሌክትሪክና የኤሌክትሮኒክስ ኢንዱስትሪ ፣ ብረታ ብረትን የሚያቀልጥና በየደረጃው የሚያክናውን ኢንዱስትሪና ፣ እነዚህን ደግሞ ወደ ማሺን በመለወጥ ለተለያዩ ኢንዱስትሪዎች የሚሆኑ መሳሪያዎችን የሚያመርት የማሽን ኢንዱስትሪ እንደሌለ በሰፊው ያብራራል። ከዚህም ባሻገር ኢትዮጵያ ከሌሎች ከሰሃራ በታች ካሉ የአፍሪካ አገሮች ጋር ስትወዳደር ያላት የቲክኖሎጂ ፈቃድ 4% ብቻ እንደሆነ ያመለክታል። ሀቁ ይህ ከሆነ ታዲያ ይህ አድጓል የሚባለው ኢኮኖሚ በምን ተዓምር ነው ሊያድግ የሚችለው? ይህ ትክክል አለመሆኑን ደግሞ የዓለም የኢኮኖሚ ፎረም በድጋሚ ያረጋግጣል።

በመሆኑም ለመጀመሪያ ጊዜ በኢኮኖሚ አሰላል ታሪክ ውስጥ የዓለም ኢኮኖሚክ ፎረም(World Economic Forum) ያነሳቸው አስራሁለት መመዘኛዎች(Pillars) ለኢኮኖሚ ዕድገት ወሳኝ ሚናን እንደሚጫወቱ ያረጋግጣል። በፎረሙም መለኪያ እነዚህ ምሰሶዎች እንደሚከተሉት ናቸው።1ኛ) ብቃት ያለው ኢንስቲቱሽኖች ፣ 2ኛ) ኢንፍራስትራክቸር ፣ 3ኛ) የማይክሮኢኖሚክ እንቫይሮንሜት ፣ 4ኛ)የህክምና ተቅዋምና የመሰረተ-ትምህርት ጉዳይ ፣ 5ኛ)ከፍተኛ ትምህርትና የቴክኒካል ማሰልጠኛ ኢንስቲቱሽን ፣ 6ኛ)ብቃት ያለው የዕቃዎች

መገበያያ ሁኔታ ፣7ኛ) ብቃት ያለው የሰራተኞች ገበያ ፣ በተለይም የሰለጠነ የሰው ኃይል ሁኔታ ፣ 8ኛ)የተቀላጠፈ የባንኮችና የፊናንስ ካፒታል ገበያና አሰጣጥ ፣ 9ኛ) ብቃት ያለው የቴክኖሎጂ ዝግጅት ፣ 10ኛ) የገበያ ስፋት ጉዳይ ፣ 11ኛ)የንግድ ውስብስብነትና መቀላጠፍ፣ 12ኛ)የፈጠራ ጉዳይ(Innovation)። ይህም ማለት እነዚህን ማሟላት የማይችል ኢኮኖሚውን ማሳደግ አይችልም ፣ ወይም በየጊዜው እየደጋገመ ኢኮኖሚው አድጓል ሊል አይችልም ማለት ነው። ከእንግዲህ ወዲያ እንደ ኢህአዴግ አገዛዝና ፣ የዓለምን ህዝብ በከፍተኛ ደረጃ የሚያሳስቱት እንደ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የመሳሰሉ ግብረ አበሮቹ እንደፈለጉት ሊጫወቱብን አይችሉም ማለት ነው። ከዚህ ስንነሳ ከላይ በሰፊው ያብራራሁትንና ፣ በተጨማሪ ደግሞ የዓለም የኢኮኖሚክ ፎረም ያስቀመጠውን የማያሟላ አገር ፣ ኢኮኖሚዬን አሳድጌያለሁ ፣ ድህነትን በመቅረፍ ላይ ነኝ እያለ በማውራት ህዝብን እንደማይደልል መረዳት ያሻል።

# የኢኮኖሚ ዕድገትና የስርዓት ጥያቄ !

ከስድሳ ወይም ከዚያ ዐመታት በላይ የዓለምን ህዝብ ያወናበደውና ግራ ያጋባው ምንም ሳይንሳዊ መሰረት መሰረት ሳይኖረው ዝም ብሎ የገበያ ኢኮኖሚ እየተባለ በጥቅሉ የሚነፍሰው አባባል ነው። በአንድ ወቅት ስለ ገበያ ኢኮኖሚ ሳትት ፣ የሰው ልጅ በአንድ ቦታ ረጋ ብሎ መቀመጥ ከጀመረና በስራ ክፍፍል መደራጀት ከጀመረ ወዲህ የገበያ ልውውጥ አስፈላጊ እየሆነ ሊመጣ ችሏል። እንደሚታወቀው ማንኛውም አምራች ግለሰብ የሚፈለገውን ነገር ሁሉ ራሱ ማምረት ስለማይችል ፣ ሌላው ያመረተውን ገዝቶ ለመጠቀም ሲል ዕቃውን ገበያ ላይ አውጥቶ ይሸጣል ፤ ይገበያያል። ይህ ሁኔታ ደግሞ ቀሰ በቀስ እያለ ለገንዘብ መፈጠርና በተለያየ መልክ መገለጽ በር እየከፈተ መጣ። በዚህ መልክ የገበያ ኢኮኖሚ መፈጠር ፣ ማደግና መስፋፋት ጀመረ። ይህ ሀተታ ግን ሙሉ በሙሉ ሳይንሳዊ አይደለም። ሳይንሳዊ ሊሆን የሚችለው ኢኮኖሚው የሚንቀሳቀስበት ስርዓት ግልጽ ሆኖ ሲተነተን ነው። ይህ እስካልሆነ ድረስ በውዥንብር ዓለም ውስጥ እንኖራለን ማለት ነው። ይህም በራሱ ደግሞ የኢኮኖሚ ዕድገት የሚለውንም ትርጉም በደንብ እንዳንረዳ ሊያደርገን ይችላል።

ይህ ችግር የመነጨውና የሚመነጨው በየትምህርት ቤቱና በየዩኒቨርስቲው የሚሰጠው የኢኮኖሚ ትምህርት ፣ ሚክሮና ማክሮ ኢኮኖሚ ፣ በጊዜ ያልተገደበ ፣ ልክ እንደ እግዚአብሄር ፣ የሰው ልጅ ፣ ተፈጥሮና ህዋ ከመፈጠራቸው በፊት እንደነበረና እንዳለ ፣ ወደፊትም እንደሚኖር ተደርጎ በብዙዎቻችን ዘንድ እንደ አመኔታ ሰለተወሰደና ስለሚወሰድ ነው። በዚህ መልክ የቀረበው የኢኮኖሚ ትምህርት ታሪካዊ ሳላይደለ ስለስርዓት ሊያወራልን አይችልም። ስለሆነም በማንኛውም አገር ፣ ብዙ ነገሮችን ፣ ለምሳሌ ስለባህልና የዕድገት ደረጃ ፣ ስለታሪካዊ አመጣጥ ፣ ስለ ጠቅላላው የኢኮኖሚ አቀነጃጀት ሁኔታና ከላይ የዘረዘርኳቸውን የቦታና የጊዜ ጥያቄ ከቁጥር ውስጥ ሳያስገባ የገበያ ኢኮኖሚ የሚለው ጽንሰ-ሃሳብና ፖሊሲው በሁሉም አገር ተግባራዊ ሊሆን ይችላል ፤ ይህም የተፈጥሮ ህግ ነው ይለናል። በዚህ መልክ ታሪክንና ባህልን ፣ እንዲሁም የህሊናን አወቃቀርና የምርት ኃይሎችን(Production factors and Production forces) የዕድገት ደረጃ ስሌትና ትንተና ውስጥ ያላስገባ ፖሊሲ ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ ከተወሳሰበ የገበያ ኢኮኖሚ ጋር ያላደጉ ህብረተሰቦችንና ፖሊሲ አውጭዎችን መቀመቅ ውስጥ ነው የሚከታቸው። የተወሳሰበና በቀላሉ ሊፈታ የማይችል የህብረተሰብ ችግር ነው የሚፈጠረው። የሰው ልጅ አቅጣጫውንና የኑሮ መመሪያ የሚሆነውን ነገር ነው እንዳያገኝ የሚደረገው። በዚህም ምክንያት ቢያንስ ባለፉት ሰላሳ ዐመታት ውስጥ በገበያ ኢኮኖሚና በግሎባላይዜሽን ስም የተካሄዱት ጣልቃ-ገብነቶችና ወረራዎች በየአገሮች ውስጥ ዱርዬነትንና የማፊያ ተግባርን ፣ የሴተኛ አዳሪዎች ብዛትና ፣ ከተፈጥሮ ህግ ጋር የማይሄዱ የፍትወ-ስጋ ድርጊቶችን ፣ የሀብት ክፍፍል መዛባትን ፣ የጥሬ-ሀብት ዘረፋንና የቆሻሻ መጣያ ቦታዎችን መስፋፋትን ፣ የቆሻሻ ቦታ ማደሪያ ቦታዎች መስፋፋት ፣ የመንግስት መኪናዎች(State Machinery) በአዲስ የመጨቆኛ መሳሪያዎች በመታጠቅና ከውጭ ኃይል ጋር በማበር በህዝብ ላይ ጦርነት ማካሄድ ፣ ባጭሩ ድህነትን ማሳፋፋት የዚህ ዐይነቱ በተሳሳተ መልክ የሚቀርብ የገበያ ኢኮኖሚ አነጋጋርና ትምህርት ነው። በመሆኑም አንድን አገር እንደ አገርና እንደ ህብረተሰብ እንዳይገነባ በማድረግ ሁሉም ነገር ካለስርዓትና ልቅ በሆነ መልክ በመካሄድ ጉልበተኛው ባሸናፊነት የሚወጣበት ፣ ደካማው ደግሞ የሚረገጥበትና እንደቆሻሻ የሚጣልበት ሁኔታን እንመለከታለን። በአገራችን የሚታየው ተጨባጩና የሚያሳዝነው ሁኔታ የዚህ የተሳሳተ የገበያ ኢኮኖሚ ውጤት ነው።ይህ በዚህ መልክ ተሳስቶ የሚነፍስ የገበያ ኢኮኖሚ አባባል እኛንም ሰለባ ስላደረገን ህዝባችንን እንድናደኸይና አገር ሻጭ እንድንሆን

አድርጎናል። ይህንን ባደረግን ቁጥር ደግሞ ሽልማት የሚሰጠንና ዝናን የምንጎናጸፍ ሆነናል። በአፍ ጢሚ የተደፋች ዓለም!!

ያም ሆነ ይህ ስለ ኢኮኖሚ ስርዓት በምናወራበት ጊዜ ስለ ምርት ኃይሎች ፣ ስለ ምርት ግኑኝነትና ፣ እነዚህ ደግሞ በምን ዐይነት ስርዓት ውስጥ እንደሚካሄዱ ማወቅ አለብን። ይህንን ስንገነዘብ ብቻ ነው ስለ ኢኮኖሚ ዕድገት ማውራት የምንችለው። እንደሚታወቀው ቢያንስ ከሰላሳ ዐመታት ጀምሮ የዓለም ኢኮኖሚዎች መለኪያ ሁሉ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ስርዓት ሆኗል። ስለሆነም ይህንን መረዳት ያስፈልጋል።

አንድ ሳናውቀው በጭንቅላት ውስጥ የቋጠርነውና እንደልማድ የወሰድነው ነገር አለ። ይኸውም ዛሬ በምዕራብ አውሮፓ ያለው ስርዓት ፣ 1ኛ) የገበያ ኢኮኖሚ ነው የሚል ፣ 2ኛ) ይህ ስርዓት  በሂደት መልክ ከብዙ መቶ ዐመታት መነሳትና መውደቅ በኋላ እዚህ ደረጃ የደረሰ ሳይሆን ፣ ትላንት የነበረ ፣ ዛሬም ያለና ነገም የሚኖር ፣ 3ኛ) ይህም የገበያ ኢኮኖሚ ስርዓት ሁሉም በእኩል ደረጃ የሚሳተፉበትና ፣ ለሁሉም ክፍት የሆነና ፣ ሁሉም ሊበለጽግበት የሚችል ስርዓት ተደርጎ ነው በሁላችን ዘንድ ግንዛቤ ውስጥ ያለው። ስለሆነም ካፒታሊዝም በምርት ግኑኝነትና በምርት ኃይሎች የሚገለጽ ሳይሆን ፣ በተራ አነጋገር በገበያ ኢኮኖሚ ብቻ የሚገለጽ ነው። ይህ ዐይነቱ አባባል በእኛ  የተለመደውን ያህል ፣ በካፒታሊስት አገሮች ግን በካፒታሊስቶችና የመንግስትን መኪና በጨበጡ እንዲያው በደፈና የገበያ ኢኮኖሚ እየተባለ የሚገለጽ ሳይሆን ፣ ማህበራዊ የገበያ ኢኮኖሚ ወይም የካፒታሊስት የገበያ ኢኮኖሚ እየተባለ ነው። አሁንም ድርቅ ብለው አይን ባወጣ መልክ ሰውን ለማሳመን በሚፈልጉት የኒዎ-ሊበራል ኢኮኖሚስቶች አመለካከት ፣ የገበያ ኢኮኖሚ በእነ አዳም ስሚዙ ዘመን እንደሚታየው በትናንሽ ከበርቴዎችና ውድድር በሰፈነበት ዘመን ዐይነት የሚካሄድ ንፁህ ኢኮኖሚያዊ ክንዋኔ ካልሆነ በስተቀር ፣ የዛሬው የገበያ ኢኮኖሚ በጣም የተወሳሰበና ፕሮፌሰር ሶዲ እንደሚሉት ግራ የሚያጋባ ነው። በዚህም መሰረት በኢኮኖሚ ክንዋኔ ውስጥ የሚሳተፍ በሙሉ እንደ አስተዋፅዖው ከፍተኛ ትርፍና ከፍተኛ ጥቅም የሚያገኝ አይደለም። በመሆኑም በተጨባጭ ዓለም ውስጥ በሚካሄደው በኢኮኖሚው ዓለምና በፎርማል ደረጃ በተጻፈው ነገር ከፍተኛ ልዩነት እንዳለ መመልከት ይቻላል።

እንደሚታወቀው የዛሬው የካፒታሊስት ስርዓት ከሶስት መቶና አራት መቶ ዐመት በፊት የነበረው ዐይነት አይደለም። የዐይነት ለውጥ የሚታይበትና ፣ በአብዛኛው ጥቂት አምራቾችኛ አቅራቢዎች(Oligolopolists) ገበያውን የሚቆጣጠሩበትና ፣ የሀብት ክምችትም በጥቂት ሰዎች እጅ የሚገኝ ነው። ይህ የስርዓቱ መግለጫ ሲሆን ፣ በመሰረቱ ካፒታሊዝም በውድድር አማካይነት የሚንቀሳቀስ ውስጠ-ኃይሉ ከፍተኛ የሆነና ፣ በተወሰነ ክልል ብቻ ሊገደብ የሚችል አይደለም። በገበያ ላይ የሚሳተፉ አምራቾችም ሆነ ነጋዴዎች በማያቋርጥ ውድድር ውስጥ የሚገኙና ፣ ከገበያ ላለመውጣት ሲሉ ወይም ደግሞ ባሸናፊነት ለመውጣት በየጊዜው የፈጠራ ክንውንና (Innovation) የቴክኖሎጂ ለውጥ ማድረግ አለባቸው። በዚህ ዐይነቱ የማያቋርጥ ውድድር የማምረቻ ዋጋን በመቀነስ ለተጠቃሚው ደግሞ በተመጣጣኝ ዋጋ ያቀርባሉ። ይህንን ለማድረግ ሲሉ ደግሞ የግዴታ አዳዲስ ማሽኖች መግዛትና መትከል ሳለለባቸው ከባንኮች ጋር በመቆላለፍ በባንክ ብድር ጥገኛ ይሆናሉ። ይህ ዐይነቱ ከታች ወደ ላይና ወደ ጎን የተቆላለፈ ስርዓትና የምርት ክንውን ለገበያ መስፋፋት የግዴታ ግፊትን ያደርጋል። ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል በገበያው ውስጥ ገብቶ ሳያውቀው ተዋናኝ ይሆናል። በኬይንስም አገላለጽ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ በገንዘብ ኃይል በሁሉም ረድፍ የተሳሰረና ፣ ገንዘብ ዛሬንና ነገን የሚያገናኝ ሆኖ በመውጣት ኢኮኖሚያዊ ሂደትን ይወስናል። እንደዚህ ዐይነቱ ኢኮኖሚያዊ ስርዓት ልዩ ስለሆነና የራሱ ህግ ስላለው ፣ ቀውሱም ልዩ ዐይነት ቀውስ ነው። በሌላ አነጋገር አሁንም በኬይንስ አነጋገር የካፒታሊስት ኢኮኖሚ እንደየሁኔታው ከፍና ዝቅ የሚል ወይም ደግሞ በልዩ ቀውስ የሚገለጽ ነው። የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ቀውስ በመሰረቱ እንደ አገራችን የስትራክቸራል ቀውስ ሳይሆን በየጊዜው ከፍና ዝቅ(Conjectural Crisis) የሚገለጽ ሲሆን ፣ ከእንደዚህ ዐይነት ቀውስ ውስጥ የሚወጣው ሹምፔተር እንደሚለው በራሱ አጥፊነትና አልሚነት(Creative Destruction) ኃይል ነው። ይህ ማለት ያረጁ ቴክኖሎጂዎች ቦታ ሳይኖራቸው ሲቀር በውድድር ዓለም ውስጥ የሚከንፈው ካፒታሊስት የግዴታ ያረጀውን ማሽን በአዳዲሶች ይተካል። ያረጁት ማሽኖች እንደየሁኔታው አይ ይጣላሉ ፣ አይ ለሌላ አገር ይሸጣሉ ፣ ካሊያም ደግሞ ሪሳይክልድ በመሆን እንደ ጥሬ-ሀብት ያገለግላሉ። ይህም ማለት የካፒታሊስት ኢኮኖሚ በማያቋርጥ ፈጠራ(Innovation) የሚገኝ ልዩ ዐይነት ኢኮኖሚያዊ ክንዋኔ ነው። ይህ ማለት ግን ገደብ የለውም ወይም ስርዓቱ ዘለዓለማዊ ነው ማለት አይደለም። ስለዚህም ስለኢኮኖሚ ዕድገት ሲወራ እንዲያው በቁጥር የሚገለጽ ብቻ ሳይሆን

በካፒታሊስት ስርዓት ውስጥ የሚካሄደውን የማያቋርጥ ለውጥ ግንዛቤ ውስጥ ካገባን የበለጠ ስለ ኢኮኖሚ ዕድገት ግንዛቤ ይኖረናል።

ወደ ብዙ የሶስተኛ ዓለም አገሮች ኢኮኖሚና ወደኛ አገር ስንመጣ ኢኮኖሚዎቹ ፤ 1ኛ) ግልጽ የሆነ የስራ ክፍፍል የላቸውም ፤2ኛ) በውድድር ህግ የሚተዳደሩ አይደለም ፤3ኛ) አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለመፍጠር የሚያስችሉ ሁኔታዎችና ኢንስቲቱሽኖች የሉም ፤ 4ኛ) የመዋዕለ-ነዋይ ደረጃዎችና ህጎች አይታወቁም ፤5ኛ) ስለሆነም በአንድ መስክ ብቻ ከፍተኛ ርብርቦሽ ይካሄዳል ፤6ኛ) ይህ በሰፈነበት ቦታ አጠቃላይ ሀብት መፍጠርና ስራ ለሚፈልገው የስራ መስክ መክፈት አይቻልም ፤7ኛ) በአንድ መስክና በተወሰኑ አካባቢዎች ብቻ የሚካሄደው የንግድ ክንውን የውስጥ ገበያን ለማስፋፋትና ለማዳበር አያመችም ፤8ኛ) በዝቅ.ህም የተነሳ የመንግስታቱ የቀረጥ መሰረት(Tax Base) የጠበበ በመሆኑ እንደልባቸው ለልዩ ልዩ ፕሮጀክቶች የሚሆናቸውን የፊናንስ ምንጭ ሊያገኙ አይችሉም። 9ኛ) የገበያ መጥበብ በራሱ በአንድ አካባቢ አርቲፊሻል የሆነ የሰውን መከማቸት ይፈጥራል ፤10ኛ) በእንደዚህ ዐይነት ሁኔታ ውስጥ ስራ ማግኘት የማይችለው ባልባሌ ቦታ እንዲሰማራ ይገደዳል ፤ ይህም ማለት ዕውነተኛ ህብረተሰብአዊ ሀብት(Social Wealth) ፈጣሪ እንዳይሆን ይገደዳል ፤ 11ኛ) የተቀረው ደግሞ ወደ ቀጣፊነት በመሰማራት ለህብረተሰቡ ጠንቅ ይሆናል ፤ ይህም ማለት በተለያየ መልክ የሚገለጽ ህብረተሰብአዊ ቀውሶች ይፈጠራሉ ማለት ነው። 12ኛ) በአሁኑ ዓለም ሃይማኖት ራሱን የቻለ አጀንዳ በመሆን ፤ የተወሰነው የህብረተሰብ ክፍል በዚህም ሆነ በዚያኛው የሃይማኖት ወጥመድ ውስጥ በመግባት የተወሰነው ከመንግስት ጋር ፍጥጫ ውስጥ እንዲገባ ይገደዳል ፤ 12ኛ) በሳይንስ ያልተጠና የኢኮኖሚ ፖሊሲና ኢኮኖሚውን በፀና መሰረት ላይ መገንባት የማይችል መንግስት የግዴታ ህብረተሰብአዊ ግፊት እንዳይመጣብኝ በማለት ሴኪዩሪትውንና የወታደሩን ወይም የፖሊስ ኃይሉን ወደ ማጠናከር ያመራል። በዚህም መሰረት ለሌላ የሶሻል ፕሮጀክት ሊውል የሚችለው ገንዘብ ወደ መንግስት ማደለቢያ በመሸጋሸግ በመንግስትና በህብረተሰቡ መሀከል ከፍተኛ መፋጠጥ ይፈጠራል። ዛሬ በአገራችንም ሆነ በብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮች የምናየው ይህን ዐይነቱን የተመሰቃቀለ ሁኔታና ፤ የየመንግስታቱን አቅመቢስነትና ወደ አውሬነት ማምራት ነው። ከዚህ ስንነሳ በተለያዩ ወቅቶች የወጡትን የኢህአዴግን ወይም የህውሃትን የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች መመልከት ይኖርብናል። ከዚያ በፊት መንግስት በካፒታሊስት የኢኮኖሚ ዕድገት የነበረውንና ያለውን ሚና መረዳት ያስፈልጋል።

## የመንግስት ሚና በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ዕድገት ታሪክ ውስጥ!

በዩኒቨርሲቲዎች በሚሰጥ የኢኮኖሚ ትምህርት ውስጥ ካፒታሊዝም እንዴት ወደዚህ ደረጃ እንደ ደረሰና ፤ ለማደግስ ምን ምን ምክንያቶች አስተዋፅዖ እንዳበረከቱ በትምህርት መልክ አይቀርብም። በሚክሮና በማክሮ ኢኮኖሚክስ መልክ ተዘጋጅተው ለትምህርት የሚቀርቡት የኢኮኖሚ መማሪያ መጽሀፎች ካፒታሊዝም እንዴት እንዳደገ ብቻ ሳይሆን ፤ ዛሬ በምን መልክ እንደሚንቀሳቀስና ፤ ውስጣዊ ባህርዩም ምን እንደሚመስል ለውይይት ወይም ለትምህርት አይቀርብም። በዚህም ምክንያት በተለይም ከሶስተኛው ዓለም አገሮች እዚህ የምዕራቡ ዓለም ዩኒቨርሲቲዎች ትምህርታቸውን አገባደው ወደ አገር ቤት ሲመለሱና በስራ ዓለም ሲሰማሩ ወይም በሚኒስተር ደረጃ ሲሰማሩ የሚሰሩት ስራ በሙሉ እነ ዓለም የገንዘብ ድርጅትና የዓለም ባንክ ያዘዟቸውን እንጂ በራሳቸው ምርምር ከአገራቸው ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች በመንደፍ አይደለም። ስለሆነም ዛሬ በብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮች ድህነትና መዘበራረቅ የሚታየው ከእንደዚህ ዐይነቱ የካፒታሊዝምን ዕድገትና ባህርይ ካለመረዳት የተነሳ ነው።

ስለ ካፒታሊዝም የህይወት ታሪክ ለማተት በጣም አስቸጋሪና ውስብስብም ነው። ይሁንና በካፒታሊስት የገበያ ኢኮኖሚ ታሪክ ውስጥ መንግስታት የተጫወቱትን ሚና መረዳቱ እጅግ አስፈላጊ ነው። ማለት ይቻላል ከ14ኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ ፤ ህብረ-ብሄሮች ከመቋቋማቸው በፊት የነበሩ ትናንሽ መንግስታት በየክልላቸው የመንግስት ኢኮኖሚ ወይም ካሜራሊዝም እየተባለ በሚታወቀው ኢኮኖሚያቸው እንዲያድግ አስፈላጊውን ሚና ተጫውተዋል። በተለይም በኢጣሊያን ፤ በአውስትሪያና በጀርመን ትናንሽ መንግስታት ዘንድ ይህ ዐይነቱ ፖሊሲ ኢኮኖሚዎችን በማደራጀት ፤ የዕደ-ጥበብ ስራዎችንና የንግድን እንቅስቃሴ በመደገፍ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። ይህንን የተመለከቱት እንደ እነ እንግሊዝ የመሳሰሉት በ16ኛው ክፍለ-ዘመን መጀመሪያ ላይ ከጣሊያን በመኮረጅ ከጥሬ-ሀብት አምራችነትና ወደ ውጭ ላኪነት በመለቀቅ በመንግስት የተደገፈ የኢኮኖሚ

እንቅስቃሴ እንድታካሄድ ተገዳለች። በዚህም መሰረትና አውሮፓ ውስጥ በተፈጠረው የሃይማኖት ውዝግብ ተጠቃሚ ሆና የወጣችው እንግሊዝ በካቶሊክ ሃይማኖት አክራሪነት ከተለያዩ የአውሮፓ አገሮች የተባረሩትን የዕደ-ጥበብና የንግድ አዋቂዎች ምሁራን በማሰባሰብና ድጋፍ በመስጠት ለኢንዱስትሪ አብዮት የሚሆናትን ሁኔታዎች በአጋጣሚዎች ታዘጋጃለች። በዚህ መልክ ወደ ውስጥ በካፒታሊዝም የሚንቀሳቀስ ኢኮኖሚ በመገንባት ወደ ውጭም የበላይነትን እየተቀዳጀች ትመጣለች። የውጭ ንግድንም ምንነት በመረዳት ደካማ አገሮች እንዲቀበሉት ትሰብካለች።

በኋላ የመጡ እንደፈረንሳይና እንደ ጀርመን የመሳሰሉ አገሮች ፣ ፈረንሳይ በ18ኛው ክፍለ-ዘመን ፣ ጀርመን ደግሞ በ19ኛው ክፍል-ዘመን አግሬሲቭ የሆነ በመንግስት የተደገፈ ፣ ግን ደግሞ በማኑፋክቱር ላይ የተመረኮዘ የውስጥ ገበያ መስፋፋት ስትራቴጂ ይከተላሉ። ይህንን ለማድረግ ንቁ የተባሉ ኃይሎችን በተለያዩ መሳሪያዎች በመደገፍ የካፒሊዝምን ዕድገት ያፋጥናሉ። አገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱትን ኢንዱስትሪዎች ከውጭ በሚመጣ ተመሳሳይ ዕቃ እንዳይዳከሙ የታሪፍ ዕገዳ ፖሊሲ ይከተላሉ። በተጨማሪም ከተማዎችን በመቆርቆርና እንዲስፋፉ በማድረግ ፣ ድልድዮችንና ካናሎች እንዲሰሩ ፣ ትምህርት ቤቶች እንዲቋቋሙ በማድረግና ህብረተሰቡ እንዲተሳሰር ልዩ ልዩ ዕርምጃዎችን በመውሰድ ለካፒታሊዝም ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርገዋል። እንደ ጀርመን የመሳሰሉት አገሮች ደግሞ በከፍተኛ ዕውቀት የተካኑ ምሁራን በመንግስት መኪና ውስጥ በመግባት ኮንሰርቫቲብ ኃይሎችን በመጋፋትና ፣ ወደ ውጭ ደግሞ ከተገለጸላቸው ምሁራን ጋር በማበር ጥበባዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ተግባራዊ እንዲሆን ይታገላሉ። በ19ኛው ክፍል-ዘመን በተለይም እንግሊዝን እየተዘዋወሩ የጎበኙ የጀርመን ልዑካን በእንግሊዙ አሰቃቂ የካፒታሊዝም ዕድገት በማዘን ወደ አገራቸው ሲመለሱ ጥበባዊ ለሆነ የኢኮኖሚ ዕድገትና ለተሰበጣጠረ የኢንዱስትሪ መስፋፋት ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ። በተለይም ከግሪኩ ስልጣኔ ጋር በመተዋወቅ ጀናራሎችና ዝቀተኛ ኦፊሰሮች ሳይቀሩ ጀርመን ምን ዐይነት የኢኮኖሚ ዕድገት መከተል እንዳለባት ፣ የመንግስትም ሚና ምን መሆን እንዳለበት ፣ ከተማዎችና መንደሮች እንዴት መገንባትና መደራጀት እንዳለባቸው ፣ ምን ምን ዐይነት የትምህርት ዝግጅቶች ለስልጣኔው እንደሚያበጁ ይመካከራሉ። ይህንንም በስራ ላይ ለማዋል ይታገላሉ። በንጉሱ ላይ ተፆኖ በማድረግ ለጀርመን አንድ መሆን አስፈላጊውን ዝግጅት በማድረግ ፣ ወደ ውስጥ በተለያዩ የጀርመን ትናንሽ መንግስታት መሀከል የግምሩክ አንድነት ስምምነት በማድረግ የውስጥ ገበያ እንዲያድግ ይደረጋል። በዚህ ዐይነቱ ግፊትና ዕውቀት ፣ ከውጭ ደግሞ በምሁራን በመደገፍና በመከራከር የጀርመን የኢኮኖሚ ዕድገት የተቃናና ፣ ሁለት ትውልድ በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ጀርመን እንግሊዝን ቀድማ ትሄዳለች። ይህ ዐይነቱ እንቅስቃሴ በዓለም ታሪክ ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ ዐይነት ለፈላስፎች ፣ ለገጣሚዎች ለደራሲዎችና ለፈጣሪዎች በሩን ይከፍታል። ከዚህ የምንማረው ምንድነው? በፈረንሳይና በጀርመን ብቻ ሳይሆን ፣ በጃፓን ፣ በአሜሪካና በደቡብ ኮርያ የየመንግስታት ሚና ፣ እንደየሁኔታው በየአገሩም ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ ፣ የውስጥ ገበያ እንዲያድግና ህዝብ እንዲተሳሰር አስፈላጊውን እርምጃ ወስደዋል። በካፒታሊስት ታሪክ ውስጥ መንግስታት ከውስጥ አገሮቻቸውን የሚያዳክም ዕርምጃ የወሰዱበትና ፣ የውስጥ ነጋዴዎችንም ሆነ የኢንዱስትሪ ባለቤቶችን የተቀናቀኑበትና ያሳደዱበት ጊዜ በፍጹም አልነበረም። በመንግስት ቁጥጥር ስር ያሉ ሀብቶች ህዝባዊ ባህርይ የነበራቸውና ያላቸው ሲሆን ፣ ከማንኛውም ፓርቲ ወይም በመንግስት መኪና ውስጥ ተቀጥሮ ከሚሰራ ሰው ቁጥጥር ውጭ ነበሩ። በአውሮፓ ታሪክ ውስጥ የመንግስት ሚና ግልጽና በህግ የተደነገገ በመሆኑ ማንኛውም የመንግስት ባለስልጣን የፈለገውን ማድረግ አይችልም።

በታሪክ ውስጥ በመንግስት የተደገፈ ፖሊሲ ተግባራዊ ማድረግ በ17ኛው ፣ በ18ኛውና በ19ኛው ክፍለ-ዘመን ሲሰራበት የነበረ ፖሊሲ ብቻ አይደለም። በሃየኛው ክፍለ-ዘመንም ሲሰራበትና መንግስታት ልዩ ልዩ ፖሊሲዎችን በማውጣት ጠንካራ ኢኮኖሚ መገንባት የጀመሩበትንም ሁኔታ እንመለከታለን። ከ1933-1945 ዓ.ም ድረስ የሂትለር አገዛዝ ያለ የሌለውን ሪሶርስስ በማንቀሳቀስ ኢኮኖሚውን ከገባበት ቀውስ ማላቀቅ ችሏል። 13 ዐመት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ትላልቅ ህንፃዎችን ፣ በአውሮፓ ውስጥ በትልቅነቱ ወደር የማይገኝለትን የአውሮፕላን ማረፊያ ሊሆን የሚችል ትልቅ ግንብ እንዲሰራ አድርጓል። ብዙ እንዱስትሪዎች እዚህና እዚያ አስተክሏል ፤ በብዙ ሺህ ኪሎ ሜትር የሚቆጠሩ መንገዶችና ድልድዮች አሰርቷል። ይህንን የምዘረዝረው አንድ አገዛዝ ፍላጎትና ዓላማ ካለው በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ነገሮችን መስራት እንደሚችል ለማሳየት ብቻ ነው። የሰውየውን የጥፋት ፖሊሲ ለመደገፍ ወይም ያደረገው ትክክል ነው ብዬ በማመን አይደለም። በተጨማሪም ይህንን የማነሳው በአደረጃጀትና በፍላጎት ማነስ እንደኛ ያለው ጥቁር ህዝብ እጅግ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንደምንገኝም ለማመልከት ነው። የኛ ችግር የድርጅት ችግር ብቻ ሳይሆን ፣ በፕሪንስፕል አለመመራትና በተቻለ መጠን ስራን ለማጨናገፍ የምንቸኩልምና ሳናውቀው አገር ወደ ማጥፋት የምናመራ ነን። ከዚህ ስንነሳ ይኸኛውን  ወይም ያኛውን የኢኮኖሚ

ፖሊሲና ቲዎሪ የመከተሉ ጉዳይ አይደለም ዋናው ቁም ነገር። ለአንድ አገር ዕድገት ድርጅትና ፍላጎት ቅድሚያውን ቦታ ይይዛሉ። ከዚህ ጋር ተደምሮ ፕሪንስፕል ያስፈልጋል። እነዚህን የማያሟላ ህዝብና አገዛዝ ወይም ፓርቲ በምንም ዐይነት ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ሊያመጣ አይችልም ፤ አይቀዳጅም።

ከዚህ ስንነሳ ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ እንደጀርመንና ፈረንሳይ የመሳሰሉት በጦርነት የተመታውን ኢኮኖሚያቸውን በ15 ዐመታት ውስጥ መልሰው መገንባት የቻሉት በተቀነባበረ የመንግስት ድጋፍና ህዝባዊ ተሳትፎ ነው። ከፍተኛ ፍላጎትና ቆራጥነት ስለነበራቸው ነው። በተንኮል ስራ በመጠመድ አልነበረም እዚህ የደረሱት። በተለይም ሁሉም ፓርቲዎች በአንድ ላይ በመቆም ተንኮል ሳይሰሩ የአገራቸውን ኢኮኖሚ መገንባት ችለዋል። እንደዚህ ዐይነቱ ቆራጥነት የበሰለ ፖለቲካና ባህልን የሚጠይቅ ነው። ከራስ በፊት አገሬና ህዝቤ መቅደም አለባቸው ብሎ የሚነሳ መሆኑን የሚያመለክትና የታሪክ ኃላፊነትን ለመሸከም ዝግጁ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው። ሁለቱም አገሮች እንደሚባለው በተራ የነፃ ገበያ አማካይነት ኢኮኖሚያቸውን አልገነቡም። ይህንን ስንመለከት በመንግስት የሚደገፈው የአገራችን ኢኮኖሚ ለምን ግቡን መምታት እንዳልቻለና እንደማይችል ጠጋ ብለን እንመልከት።

## የኢህአዴግ የኢኮኖሚ ፖሊሲ በመጀመሪያው ወቅት!

ከሁለት ዐመት ተኩል በፊት የወጣውን የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ፖሊሲ ለመረዳት ኢህአዴግ ቀደም ብሎ 18 ዐመት ያህል የተከተለውን የኢኮኖሚ ፖሊሲና የቲዎሪ መሰረቱን ወይም ፍልስፍናውን መረዳት ያስፈልጋል። በአገራችን ውስጥ ቲዎሪም ሆነ ፖሊሲዎች ከሳይንስ አንፃር ስለማይመረመሩ ፣ ሁሉም በአንድ ድምጽ የፖሊሲ ስህተት ነው እያለ ብቻ ነው የሚያወራው። ለምን የፖሊሲ ስህተት እንደሚኖርና ፣ ለምንስ በዚህ መልክ ድህነትና ህብረተሰብአዊ መዘበራረቅ እንደሚፈጠር ጠለቅ ብሎ ለመመራመርም ሆነ ደፍሮ ለመከራከር የሚቃጣ የለም። በአውሮፓ ታሪክ ውስጥ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ከውጭ በመቀዳት እንዲያው በአቦሰጡኝ ተግባራዊ የሆኑበት ጊዜ በፍጹም አልነበረም ፤ የለምም። አንዱ ከሌላኛው ሲኮርጅ በደንብ በመመርመርና ለአገሩ የሚያዋጣና የማያዋጣ መሆኑን በሰፊው ካጤነ በኋላ ብቻ ነው ተግባራዊ የሚያደርገው። በዚህ ረገድ ጀርመኖች የእነ አዳምስሚዝን የኢኮኖሚ ቲዎሪና የኢኮኖሚ ፖሊሲ በመቃወም የራሳቸውን አውጥተዋል። ቁጥራቸው የማይታቅ በራሳቸው ጭንቅላትና ነፃነት የሚያስቡ ኢኮኖሚስቶችና ምሁራን ተፈጥረዋል። ወደኛ አገር ስንመጣ ግን አሳዛኝ ሁኔታ እንመለከታለን።

ያም ሆነ ይህ ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ በኋላ በሁሉም ዘንድ አንድ ዐይነት ስምምነት ነበር። ይኸውም የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በገበያ ኢኮኖሚ መርህ ላይ መዘጋጀት አለበት የሚል ነው። በብዙዎቻችንና በዓለም ኮሚኒቲው አመለካከትም ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ ጀምሮ የደርግ አገዛዝ ይከተል የነበረው የዕዝ ኢኮኖሚ ወይም የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ነበር የሚል ነው። ይሁንና ግን የት ቦታ ላይና እስከምን ድረስ የደርግ አገዛዝ በጥቅሉ የዕዝ ኢኮኖሚ ይከተል እንደነበር የመረመረ አልነበረም ፤ የለምም። በሌላ ወገን ግን ደርግ ስልጣን ላይ ከወጣ ጀምሮ የወሰዳቸው የናሽናላይዜሽን ፖሊሲዎች እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ ትክክል መሆናቸውን የሚክድ ካለ በጊዜው የነበረውን የኢትዮጵያን ሁኔታ በፍጹም አልተረዳም ማለት ነው። በ18ኛውና በ19ኛው ክፍለ-ዘመን በጀርመን ምድር ፣ በተለይም በፕረሽያ መሬት በባላባቶች የተያዘ ስለነበረና ፣ የገበሬውም ኑሮና ስራ እጅግ አስቸጋሪና አሰቃቂ ስለነበር ፣ በአጠቃላይም ሲታይ መሬት በጥቂት ባላባቶች ስር መዋሉ ለኢኮኖሚ ዕድገት አመቺ ስላልነበር ይህ መስተካከል እንዳለበት ስለታመነ የማሻሻያ እርምጃ ተወስዷል። እስከተወሰነ ደረጃም ድረስ ተግባራዊ ሆኗል። በሌላም መስኮች በጊዜው ስልጣን ላይ የነበረው የንጉስ ፍሪድሪሽ ትልቁ መንግስት የጥገና ለውጦችን አካሂዷል።

ወደ አገራችን ስንመጣ ይህ ዐይነቱ እርምጃ ቀደም ብሎ ስላልተወሰደና ንጉስና አሪስቶክራሲው ፊቃደኛ ስላልነበሩ የየካቲቱ አብዮት ሊፈነዳ ቻለ። የመጀምሪያውና ዋናው ጥያቄ የመሬት ላራሹን ተግባራዊ ማድረግ ነበር። ይህ ጉዳይ ጭቆናን ከማስወገድ ብቻ ሳይሆን ከኢኮኖሚ ዕድገት አንፃርም ታስቦ ለመሆኑ የማይካድ ሃቅ ነው። ይሁንና ግን በአፈጻጸምና ፣ ራሱ ፕሮግራሙም በጣም ራዲካል ስለነበር ብዙ ቅሬታን በማስከተል እስከ ጠብመንጃ መማዘዝ ድረስ ተደርሷል። እርምጃውን የሚቃወሙ የውስጥና የውጭ ኃይሎች ድርጊቱን ከሶሻሊዝም ጋር በማያያዝ የአገራችንን ሁኔታ ወደ ማመሰቃቀል ገቡ። ተቃዋሚው የውስጥ ኃይል ቢያንስ ከኢኮኖሚ ዕድገት አንጻር ሊኖረው የሚችለውን አስተዋፅዖ ባለመረዳቱ በጊዜው በአብዮቱ ላይ ቢዘምትም ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ከወታደሩ አገዛዝ የተወሰደው ከውይይት ይልቅ የወታደር ኃይል እርምጃ ስህተት መሆኑንም መገንዘብ ያስፈልጋል። በተጨማሪም በጊዜው ስልጣን ላይ የነበረው የወታደር አገዛዝ ምሁራዊ ኃይሉ

እስከዚህም ድረስ ስላለነበር በውይይት ለማሳመን እንደማይቻል አንዳንድ ፍንጫዎች ያመለክታሉ። ስለሆነም ደርግ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ህግን የተረዳና በየቅደም ተከተሉ መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች ማውጣትና ማውረድ የሚችል ነበር ብሎ መናገር ያዳግታል። ያም ሆነ ይህ ድርጊቱን በጭፍን ከኮሚኒዝም ጋር ማዛመዱ እስከዛሬም ድረስ በዚህ ዐይነቱ ዘመቻ ውስጥ በመካፈል በሆነው ባልሆነው ለዕድገት የሚደረገውን ትግል በማደናቀፍ ላይ ይገኛል። በተለይም መሬትን ግላዊ የማድረጉ ወይም የመሸጡና የመለወጡ ጉዳይ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት በማግኘቱ ወደፊት ለውይይት የሚቀርቡ አጀንዳዎች እንዳሉ ካሁኑ መረዳት ያሻል። በዚህ ላይ በጥሞና መከራከር ብቻ ሳይሆን ፣ በምን ዐይነት መልክ እንደሚፈታ ፣ በተለይም ከኢኮኖሚ ዕድገት አንፃር ብቻ ሳይሆን ከህብረተሰባዊ መረጋጋትም አኳያ ምን ምን ቢደረጉ ይሻላል በሚለው ላይ ለማሳመን የሚቻሉባቸው ነጥቦች አሉ። ያም ሆነ ይህ በጭፍኑ ተነስተን አንድን ስርዓት ሶሻሊስት ነው እያሉ መወንጀልና የማያስፈልግ አቋም መወሰድ ለክርክርም ፣ ለጥናትና ሃሳብ ለሃሳብ መለዋወጥ አመቺ አይደለም።

ኢህአዴግ በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና በዓለም ባንክ የረቀቀውን የኒዎ-ሊበራል ፖሊሲ ሲቀበል ፣ በጥናቱ መሰረት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ 85% የሚሆነው ከእጅ ወደ አፍ በሚካሄድ አስተራረስ ላይ የተመረኮዘና እዚህና እዚያ ተሰበጣጥረው የሚገኙ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ወሳኝ ሚናን ይጫወቱ እንደነበር የተደረሰበት ጉዳይ ነው። ይህም ማለት እንደተባለው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በደርግ ዘመን ሶሻሊስታዊ አልነበረም ማለት ነው። ያም ሆነ ይህ የገበያ ኢኮኖሚ አስፈላጊ ነው ተብሎ በፖሊሲው መሰረት አንድ በአንድ የማክሮ ኢኮኖሚክ ኢንስትሩሜንትስ የተባሉት ስራ ላይ ይውላሉ። የውጭ ካረንሲውን ዝቅ ማድረግ ፣ የመንግስትን ሀብት ወደ ግል ማዛዋወር ፣ የውጭውንና የውስጡን ገበያ ልቅ ማድረግ ፣ ለውጭ አገር ኢንቬስተሮች አመቺ ሁኔታን መፍጠር የመሳሰሉት ተግባራዊ ቢሆኑ በኢትዮጵያ አየር ላይ የገበያ ኢኮኖሚ በማንዣበብ የኢትዮጵያ ህዝብ ከዘመናት ድህነት ይላቀቃል ተብሎ ነው የተነገረን። በሌላ ወገን ግን በዓለም የአቀፍ የገንዘብ ድርጅት ተጠንቶ የቀረበውን ዘገባና የፖሊሲ እርምጃ ለተመለከተ በምንም ዐይነት ሳይንሳዊ ነው የሚያሰኘው አልነበረም። በዚህም ምክንያት ፖሊሲው ተግባራዊ ሲሆን ኢኮኖሚውን ከማሳደግ ይልቅ በከፍተኛ ደረጃ የሚያዛባ ሆነ። በመሆኑም ፖሊሲው ተግባራዊ ሲሆን ተጠቃሚው በነጻ የሚንቀሳቀሱ የአገር ውስጥ ነጋዴዎችና ከበርቴዎች ሳይሆኑ ፣ ከህውሃት ጋር የተቆላለፉ ግለሰቦችና አንድ ድርጅት ነው የመንግስትን ሀብት ወደ መቆጣጠር ያመሩት። በጊዜውም በቀላሉ ከባንክ ብድር ያገኙ የነበሩት ሰዎችም እነሱ ነበሩ። ይህም ማለት ምን ማለት ነው? ግልጽ የሆነ የመንግስት አወቃቀርና የህግ የበላይነት በሌለበትና ፣ እንዲሁም ንቃተ-ህሊናው በዝቅተኛ ደረጃ በሚገኝበት አገር የገበያ ኢኮኖሚ የሚባለው መርህ ተግባራዊ ሲሆን እንደሚባለው የኢኮኖሚ ዕድገት ይታያል ማለት ሳይሆን ፣ የተገላቢጦሽ ድህነትንና ጥገኝነትን መጎናፀፍ እንደሚቻል የአገራችን ተጨባጩ ሁኔታ በሚገባ አረጋግጧል። ይህም ማለት በፍልስፍናው መሰረት ነጻ ውድድር ለማድረግ የማይቻልበት ሁኔታ ነው የተፈጠረው። በዚህም ምክንያት መንግስት ለሁሉም እንደ ችሎታው አመቺ ሁኔታዎችን ከመፍጠርና ትምህርት እየሰጠ የአገር ውስጥ ከበርቴ እንዲያድግ አስፈላጊውን እንክብካቤ ከማድረግ ይልቅ ራሱ ከጥቂቶች ጋር በማበር የገበያ ወይም የካፒታሊስት ኢኮኖሚ እንዳይስፋፋና እንዳይዳብር ለማገድ ቻለ። ይህ ራሱ የሀብት ክምችትንና እንቅስቃሴን በተወሰኑ ቦታዎችና በተወሰኑ ግለሰቦች እጅ ብቻ እንዲካሄዱና እንዲከማቹ አደረገ። በአጭሩ የእነ ዓለም የገንዘብ ባንክ ድርጅት የኢኮኖሚ ፖሊሲ በአገራችን ውስጥ በሁሉም መስክ የሚታይ መዛባትንና ህብረተሰብአዊ መመሰቃቀልን ሊያስከትል ቻለ።

ከዚህ ስንነሳ በእነ አይ ኤም ኤፍና በአጠቃላይ በዓለም ኮሚኒቲው የሚደገፈውን በአገራችን ተግባራዊ የሆነው ፖሊሲ በታሪክ ውስጥ በሌሎች አገሮች እንደታየው ዐይነት የኢኮኖሚ ዕድገት ያመጣ ሲሆን የውስጥ ገበያ እንዳይስፋፋ ያገደ ነው። ሀብትን መቆጣጠር የቻሉት ጥቂት ሰዎችና አንድ ድርጅት ከታሪክ አንፃር ራሳቸው ፈጣሪዎችና የስራ መስክ አመቻቾች ስላልሆኑ ያመሩት ንጹህ የገንዘብ ካፒታልን ማከማቸት ፣ ወደ ሪል ስቴት መሰማራትና ፣ ስትራቴጂክ የሆኑ እንደ ሰሊጥና ቡናን የመሳሰሉ የጥሬ-ሀብቶችን ወደ መቆጣጠር ነው። በዚህም ምክንያት እነዚህ ሰዎች ወደ ክላሲካል አቀባባይ ከበርቴነት በመሸጋገር የአገር ዕድገትን ከማጨናገፍ ባሻገር ከውጭ የሚመጣ የፍጆታን ዕቃ በመጠቀም ልዩ ዐይነት ግን ደግሞ ጎታች የሆነ ባህልን ማስፋፋት ቻሉ። ይህም ማለት የውስጥ ኃይላቸው በጣም ደካማና ለአጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገት ያላቸው አስተዋፅዖ በጣም የመነመነ ነው ማለት ይቻላል።

ይህ ዐይነቱ የኢኮኖሚ ክንዋኔና ሂደት በአገልግሎት መስኩም አይሎ ስለሚታይ ብዙ ሀብት ወደዚህ አካባቢ እንዲፈስ አድርጓል። ስለሆነም እንደዚህ ዐይነቱ ውስጠ-ኃይሉ

በጣም ደካማ የሆነ ኢኮኖሚ ድህነትን ፈልፋይ ከመሆን ባሻገር አዳዲስ የሰራ መስክን በመፍጠር ድህነትን እንዲቀረፍ የሚያስችል አይደለም። በተቃራኒው በአዲስ አኗኗር የተካነው አዲሱ መጤ ከበርቴ ለኑሮ ውድነት ተጠያቂ በመሆን ለሰፊው ህዝብ አስቸጋሪ ሁኔታ ነው የፈጠረለት። የአገሪቱን የኢኮኖሚ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ ሳያስገቡ እዚህና እዚያ የሚሰሩት ሆቴል ቤቶች ፣ መብራትና ውሃን እንዲሁም ምግብን ተጋሪ በመሆናቸው በህዝቡ የኑሮ ሁኔታ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አስከትለዋል። በዚህም የተነሳ ዛሬ አገራችን ከሆቴል ቤቶች የሚለቃቀሙ ፍርፋሪዎች የሚሸጡባት አገር ሆናለች። ይህንን በእነ አይ ኤም ኤፍ የተደገፈውን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ያመጣውን አሉታዊ ውጤት ለመቅረፍ እየተባለ በየጊዜው አዳዲስ የድህነት ቀራፊ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ወጥተዋል። እነዚህ ፖሊሲዎች አንድም ቦታ ላይ ድህነተን ሲቀርፉና የህዝቡን ኑሮ ሲያሻሽሉ በፍጹም አልታዩም። በአንፃሩ የአውሮፓ መንግስታት ለብቻው ድህነትን ለመቀረፍ በሚል የተከተሉት ፖሊሲ በፍጹም አለነበረም። ሲነሱ ፖሊሲያቸው ሁለ-ገብና(Holistic) ለአንዴም ለመጨረሻም ጊዜም ድህነትን የሚያጠፋ ነበር። ይህም ማለት ስርዓት ያለው በሁሉም መልክ የሚገለጽ የኢንዱስትሪና የእርሻ ፖሊሲ እንዲሁም የከተማዎች ግንባታ ፖሊሲ ማካሄድ ነው የጀመሩት። በተጨማሪም ራስን በምግብ መቻል አለብን በማለት ነው የእርሻውን መስክ ማስተካከል የጀመሩት። በተለይም በ18ኛው ክፍለ-ዘመን የነኮልበርት መንግስት ዋናውና ተቀዳሚ ፖሊሲ በምግብ ራስን መቻልና ህዝቡን መመገብ የሚል ነበር። ምክንያቱም ቀላል ነው። አንድ ህዝብ በበቂ ሲመገብና አስፈላጊውን ለሰውነቱ ግንባታ የሚያስፈልጉትን ምግቦች ሲያገኝ ለስራ ያለው ፍላጎት ይነሳሳል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ዕውቀትን ማስፋፋት ፣ ለዕድገትና ለስልጣኔ የሚያመቹ ኢንስቲቱሽኖችን ማቋቋምና ዘመናዊ ማድረግ ነበር ዋናው ዓላማቸው። በተቃራኒው ግን እነ ዓለም የገንዘብ ድርጅት ፣ ቀጥሎ ደግሞ የተባበሩት መንግስታት በሚሌኒዬሙ ፕሮግራም ያወጧቸው ፖሊሲዎች ማታለያና ድህነትን ማራዘሚያ ናቸው። ምስኪኑን ድሃ ህዝብ ራሱን እንዳይችልና ነጻ እንዳይወጣ የሚያደርጉ ናቸው። ስለሆነም አገራችንም በዚህ ዐይነቱ አስቀያሚ ሁኔታ ውስጥ በመገኘት አሁንም በድህነት መለኪያ መሰረት የመጨረሻ ደሃ ከሚባሉት አገሮች ተካታ መቀለጃ የሆነችው በዚህ ዐይነቱ መቀለጃ ፖሊሲ አማካይነት ነው። ይህ የአገዛዙ ድክመት ብቻ ሳይሆን ፣ እዚህና እዚያ የሚራወጠው ምሁር ባይኝም ድክመት ነው። እነ አይ ኤም ኤፍን እንደ አምላክ ስለሚቆጥራቸው በነሱና በአገዛዙ መሀከል ያለውን መቆላለፍ በመካድ የአገራችን ችግር ውስጣዊ ችግር ብቻ ሆኖ ይቀርባል። በዚህም ምክንያት የእነ አይ ኤም ኤፍ ፖሊሲ ሊታለፍ እንደማይችልና ፣ የዓለም አቀፍ አገዛዝን አመራር ፖሊሲ መቀበል እንዳለብን በተዘዋዋሪ ይነገራል።

ያም ሆነ ይህ የአገራችን የኢኮኖሚ ሁኔታ ባጭሩም ቢሆን ከላይ በተመለከተው ሁኔታ መታየት ሲኖርበት ፣ አገዛዙ ከ18 ዐመት የገበያ ኢኮኖሚ ፖሊሲ በኋላ ለምን ወደ ዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ፖሊሲ እንዳመራ ደግሞ እንመልከት።

## የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ፖሊሲ ምንነትና

## ተግባራዊ የመሆን ችግር!

የዕድገትና የትራንስፎርሜሽኑ ዕቅድ ከረዥም ጊዜ አኳያ የአነፃፀረውን ዋና ዓላማ በሁለት መሰረታዊ ነገሮች ያስቀምጣቸዋል። ይህም በቻፕተር 2 በገጽ ሰባት ላይ ከታች በተመለከተው መልክ ሰፍሯል።

Ethiopia`s long-term vision is

> “**to become a country where democratic rule, good-governance and social justice reigns, upon the involvement and free will of its peoples; and once extricating itself from poverty and becomes a middle-income economy.”**

Its vision in the economic sector is

> “ **to build an economy which has a modern and productive agricultural sector with enhanced technology and an industrial sector that plays a leading role in the economy; to sustain economic development and secure social justice; and, incrase per capita income of citizens so that it reaches at the level of those in middle-income countries.”**

የዕቅዱ ዋና የረዥም ጊዜ ዓላማ እንደዚህ ቁልጭ ብሎ ከተቀመጠ ፣ እስካሁን ድረስ የኢህአዴግን የኢኮኖሚ ፖሊሲ እንደተመለከትነው ይኸኛውንስ ተግባራዊ ሊያደርግ

የሚያስችለው ፍላጎትና የሚመራበት ፊሎሶፊ አለው ወይ? ብለን መጠየቅ ይኖርብናል። አገዛዙ በዚህ የረዥም ጊዜ ዓላማ ብሎ በነደፈው ውስጥ የማዕከለኛ ገቢ አላቸው የሚባሉ አገሮች እስካሁን ኢህአዴግ የሙጥኝ ብሎ የተጓዘበትን መንገድ ይዘው ነው ሊደርሱና ብሄራዊ ኢኮኖሚ ሊገነቡ የቻሉት ወይ? ሲነሱስ ብሄራዊ አጀንዳቸው ምን ነበር? አገራቸውን በክልሎች በመከፋፈልና ርዕይ እንዲያጡ በማድረግ ነው ወይ ወደ ማዕከላዊ ገቢ ኢኮኖሚ ሊያመሩ የቻሉት? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው። እነዚ ከላይ የሰፈሩት ግቦች ለምን ተግባራዊ ሊሆኑ እንደማይችሉ ከላይ በሰፊው የአብራራሁ መሰለኝ። አሁን ደግሞ ወደ አንዳንድ ዝርዝር ጉዳዮች ላይ ለምራ።

በመጀመሪያ ደረጃ ወደ ቁም ነገሩ ጠለቅ ብለን ከመግባታችን በፊት የፅንሰ-ሃሳቦችን ትርጉም እንመልከት። ዕድገት ማለት ሁለንታዊ ብቻ ሳይሆን ኦርጋኒክ ነው። ይህም ማለት አስፈላጊው ሁኔታዎች ከተሟሉ ወደ ታችና ወደ ላይ ፣ እንዲሁም ወደ ጎንም ሊስፋፋ የሚችል ነው። ይህ ማለት ግን ገደብ የለውም ማለት አይደለም። አንድ ፍሬ የሚሰጥ ዛፍ ሲተከል ፣ ለምሳሌ ቡና ወደ ስርና ቀስ በቀስ ወደ ላይ በማደግና ቅጠል በማውጣት ከአራት ዐመት በኋላ ፍሬ ይሰጣል። ሌሎችንም እንደዚህ መመልከት ይቻላል። ይህንን ወደ ኢኮኖሚ ዕድገት ስናዘዋውረው ፣ ከላይ ስለ ካፒታሊዚም ዕድገት በመጠኑ ስትነትን ፣ አንድ በደንብ የተቀናጀ ፖሊሲ ሁለንታዊ እንደሆነና ወደ ሁሉም አቅጣጫ በመስፋፋት የገበያ ኢኮኖሚ የሚባለውን ነገር እንደሚፈጥር ነው። በዚህም ረገድ አንደኛው የኢኮኖሚ ዘርፍ ከሌላው ጋር በመተሳሰርና በመደጋገፍ ልክ እንደሰውነታችን የደም ዝውውር በመንቀሳቀስ ያድጋል። በውድድር አማካይነት ያረጀው በአዲስ በመተካት ውስጠ-ኃይሉ ከፍ እያለ ይሄዳል። በሌላ አነጋገር የኢኮኖሚ ዕድገት በተወሰኑ ነገሮች ፣ በተለይም በስኳር ፋብሪካ ተከላ ፣ በቢራ ፋብሪካና በሆቴል ቤት ስራዎች ብቻ የሚገለጽ አይደለም። እንደሚታወቀው ደግሞ እነዚህ ፋብሪካዎች ከውጭ እየመጡ የተተከሉና ፣ በየሆቴል ቤት ግንባታዎች ውስጥም ከውጭ ያለቀላቸው ዕቃዎች ፣ እንደመስታወትና እንደ መዝጊያና መስኮቶች የመሳሰሉት ፣ በኢንዱስትሪዎች ውስጥም በግማሽ መልክ የተፈበረኩ የጥሬ-ሀብቶችና ሌሎች የመለዋወጫ ዕቃዎችም እንዳሉበት ማጤን ያስፈልጋል። በእርግጥ እነዚህን ያገሪቱ ውጤት ያልሆኑትን ከደመርን ስለኢኮኖሚ ዕድገት ማውራት ይቻላል። ያም ሆነ ይህ እነዚህ በራሳቸው የአንድ አገር ኢኮኖሚ ዕድገት መግለጫዎች አይደሉም።

ወደ ትራንስፎርሜሽን ወደሚለው ፅንሰ-ሃሳብ እንምጣ። ትራንፎርሜሽን ማለት ሁለንታዊ ለውጥ ማለት ነው። ወደ ህብረተሰብ ሲለወጥ ለምሳሌ የፊዩዳሊዝምን ወደ ካፒታሊዝም መሸጋገር ወይም መለወጥ መመልከት ይቻላል። በዚህ ረገድ በስድሳኛውና በሰባኛው ዐመተ ምህረት የፊዳዩሊዝምን ወደ ካፒታሊዝም መሸጋገር የጦፈ ክርክርና ጥናት ተካሂዷል። ለማንኛውም ስልትራንስፎርሜሽን ስናወራ ፣ ማቴሪያላዊ ፣ ሃሳባዊና መንፈሳዊ ፣ ኢንስቲቱሺናዊና ሌሎች ነገሮችን ፣ ለምሳሌ እንደ ትምህርት የመሳሰሉትንም የሚያካትት መሆን አለበት። በታሪክ እንደታየው ካለ ሬናሳንስ ፣ ካለ ሪፎርሜሽንና ካለ ኢንላይትሜንት እንቅስቃሴ ፣ ከዚህም ባሻገር ካለሳይንስና ካለቴክኖሎጂ ግኝት ትራንስፎርሜሽን ሊኖር እንደማይችል የአውሮፓው ታሪክ ያስተምረናል። ይህ ብቻ ሳይሆን የአውሮፓን ታሪክ ላነበበ ፣ መጀመሪያ እንዱስትሪዎች እዚህና እዚያ ከመተከላቸው በፊት ፣ በጊዜው አይቻልምም ፣ በመጀመሪያ ደረጃ የሚያማሩ ከተማዎችን መገንባት ፣ የዕደ-ጥበብ ሙያዎችንና ንግድን ማስፋፋት ፣ ትላልቅ ቤተክርስቲያናትንና ቤተመንግስቶችን መስራት ለለውጥ አመቺ ሁኔታ እንደፈጠሩ ምርምሮች ያረጋግጣሉ። እነ ኮፐርኒከስና ጋሊሌዮ በተዓምር የተፈጠሩ ሰዎች ሳይሆኑ በጣም አመቺው ሁኔታ የፈጠራቸው ናቸው። በዚህ ላይ በጊዜው በአዳዲስ ስራዎች የተማረኩ ነገስታት ለሳይንስና ለለውጥ አመቺ ሁኔታዎች ፈጥረዋል። ወደ እንግሊዝም ስንሄድ ፍራንሲስ ባኮንና ኒውተን ካለምክንያት የተፈጠሩ አይደሉም። አመቺው ሁኔታ የወለዳቸውና ሁኔታውን በመጠቀም ጥልቅ ምርምር በማድረግ ለኛ ሁሉ የሚሆን የሳይንስ ግኝት ያደረጉ ታላላቅ ሰዎች ናቸው።

ከዚህ ስንነሳ የኢህአዴግ የትራስፎርሜሽን ፖሊሲ እጅና እግር የሌለው ነው። ዝም ብሎ አስፈላጊውን የምሁራዊ እንቅስቃሴ እርምጃና ሁለንታዊ የሆነ የኢንስቲቱሽን ግንባታ ሳያካሄድ እንዲያው በአየር ላይ የሚካሄድ ይመስል ዝም ብሎ የሚወራ ፕሮፓጋንዳ ነው። ትራንስፎርሜሽኑ በአዲስ ሰዎችና አዲስ ሃሳብ ባለቸው ፣ እንዲሁም ፍላጎትን በተላበሱ ሊካሄድ የታለመ አይደለም። ሃያ ዐመት ያህል ኢትዮጵያን ሲኮረኩሟትና ሲያደቋት በነበሩ ሰዎች ነው እንዲካሄድ የታሰበው። ይህ ብቻ አይደለም ፤ በዕድገትና በትራንስፎርሜሽን ታሪክ ውስጥ ከውጭ የሚመጣ አሳብና መዋዕለ-ነዋይ አስፈላጊ ቢሆንም ፣ በታሪክ ውስጥ እንደታየው የአንድ አገር ዕድገት ተሸካሚና አራማጅ ኃይል የአገሬው ህዝብ ነው። ከውጭ የሚመጡ ኢንቬስተሮች-በጊዜው ይህ ቃል አይታወቅም ነበር- እዚያው አገር ውስጥ ለመኖር የሚችሉና ለጠቅላላው ኢኮኖሚና የህብረተሰብ

ዕድገት አስተዋፅዖ ማድረግ የሚችሉ ነበሩ ፤ መሆንም አለባቸው። በጣሊያን በ13ኛው ክፍለ-ዘመን ፣ በእንግሊዝ በ16ኛውና በ17ኛው ክፍለ-ዘመን ፣ በጀርመን ደግሞ በ18ኝውና በ19ኛው ክፍለ-ዘመን ከውጭ አዋቂዎችንና የዕደ-ጥበብ ሰራተኞችን እያስመጡ ማስፈርና ህብረተሰብአዊ አካል እንዲሆኑ ማድረግ የተለመደ አሰራር ነበር። ስለዚህም እነዚህ ከውጭ የመጡ ኃይሎች የበላይነት ሳይሰማቸው አጠቃላይ የሆነ የህብረተሰብ ሀብት ለመፍጠር ችለዋል። ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ ግን ኢንቬሰተሮች እየተባሉ የሚገቡትና ትላልቅ የእርሻ መሬቶች የሚሰጣቸው ንጹህ ዘራፊዎች ናቸው። ፀረ-ዕድገቶች ናችው። ህብረተሰብ እንዳንመሰርትና የቴክኖሎጂ ባላቤት እንዳንሆን የሚያደርጉን ናቸው። ተበጣጥሰንና ብዥ ብሎብን እንድንኖር የሚያደርጉን ናቸው። በስነ-ስርዓት የሚደራጅ ባህላዊና ለጠቅላላው ህዝብ የሚጠቅም የኢንዱስትሪ ፖለቲካ እንዳይካሄድ እንቅፋት የሚፈጥሩ ናቸው። ህብረተሰብአዊ ሰንሰለትና ልዩ ዐይነት ባህል እንዳይዳብር የሚያግዱ ናቸው። በዘለዓለማዊ ድህነት እየማቀቅንና እየተሳቀቅን እንድንኖር የሚያድረጉን ናቸው። ነፃነታችንና ማንነታችንን የሚገፉ ናቸው። በመሬታችንና በተቀደሰቹው ተፈጥሮአችን ላይ ዘመቻ የሚያደርጉ ናቸው። ዛፎቻችን እንዲቆረጡ ፣ ውሃዎቻችን እንዲመረዙና ፣ በጠቅላላው የአካባቢ ሁኔታ እንዲዛባ የሚያደርጉ ናቸው። በዚህ መልክ ሳይንስና ቴክኖሎጂዎችን መቀዳጀትና ማዳበር በፍጹም አይቻልም። ይህ ለማንኛውም ግልጽ መሆን ያለበት የኢኮኖሚና የህብረተሰብ ግንባታ ሀሁ ነው። አገርን አሰለጥናለሁ ፣ ወደ ሌላ ደረጃ አደርሳለሁ ከሚል መውጣት የሚገባው አይደለም።

ችግሩ ይህ ብቻ አይደለም። የኢህአዴጉ የትራንስፎርሜሽን ፖሊሲ ከየት ወደየት እንደሚወሰደን አይነግረንም። ያለንበት ስርዓትም ምን እንደሆን አይነግረንም። ዝም ብለን ብቻ መኪና ውስጥ ገብተን እንጓዝ ነው የሚለን። ወደ ካፒታሊዝም ነው ፣ ወደ ገበያ ኢኮኖሚ ወይስ ወደ ሶሻሊዝም ፣ ወይስ ደግሞ ስርዓቱ ወደ አልታውቀ ነው የሚወስደን። ይህ ግልጽ እስካልሆነ ድረስ አስር ጊዜ የተለያየ ስም እየተሰጠው የሚወጣ ፖሊሲ የባሰ ውዥንብር ውስጥ ነው የሚከተን። ትዝ እስከሚለኝ ድረስ የዛሬ ሰባት ወይም ስምንት ዐመት ገዳማ እዚህ ጀርመን አገር የመጡ የመንግስት ልዑካን ኤምባሲ ውስጥ በሰጡት መግለጫ ፣ መንግስታቸው የሁሉኑም አገር የኢኮኖሚ ፖሊሲ ከመረመረና ካየ በኋላ አሁን የጀርመኑን ሞዴል ለመከተል እንደወሰነ ነበር የነገሩን። ከጥቂት ዐመታት በኋላ ከቻይና መንግስት ጋር ሸር ጉድ ሲባል የቻይናውን መንገድ ነው የምንከተለው አሉን። ይህ ሳይባቃ ሰሞኑን ስለ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የሁለት ዐመት ተኩል ውጤት ገለጻ የሰጡት የገንዘብና የልማት ሚኒስትሩ አቶ ሱፊያን አህመድ የደቡብ ኮሪያውን ሞዴል ነው ለመከተል ያሰብነው አሉን። ይህ የሚያመልክተው ከፍተኛ ውዥንብርና የምሁር ክፍተት እንዳለ ነው። ፖሊሲ አውጭዎቹ ምን እንደሚሰሩ አያውቁም ማለት ነው።

ያም ሆነ ይህ ፖሊሲው አሁንም የኢህአዴግን ፣ በተለይም የህውሃትን የበላይነት የሚያጠነክር ነው። በምንም ዐይነት ከውስጥ ሆነው በነፃ ለመንቀሳቀስ የሚፈልጉና ጊዜ የሚጠባበቁ የአገር ቤት ኢንቬስተሮች መፈናፈኛ የሚሰጥ አይደለም። የውስጥ ገበያ እንዲስፋፋና እንዲገነባ የሚያግዝ አይደለም። አሁንም ኢትዮጵያ የቡና ፣ የስኳርና የሰሊጥ አምራች በመሆን ለኢንዱስትሪ አገሮች የጥሬ-ሀብት አቅራቢ ሆና እንድትቀር የሚያደርግ ነው። የሃያ አንድ ዐመቱን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ስንመረመር በክልሎች መሀከል ትልቅ ልዩነት እናያልን። ዘጠና በመቶ በሚሆነው የአገሪቱ ግዛት ውስጥ ዘመናዊ የሆነ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ሲካሄድ አይታይም። የልማትና የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ በየክፍለ-ሀገራቱ ምን ምን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች እንዳሉና እነሱንም እየተዘዋወሩ የጎበኙና የሚጎበኙ አይደሉም። ለምሳሌ ብዙዎች የድሮዎቹ የክፍለ-ሀገራት ከተማዎች ወደ መንደርነትና ወደ ጨኤት መቃሚያነት እንደተለወጡ እንሰማለን ፤ እንመለከታልን። ቢሮዎች የመመራመሪያና የፖሊሲ አውጭ መስሪያቤቶች ከመሆን ይልቅ ወደጨአት መቃሚያነት ተለውጠዋል። በየአካባቢው ዕድገትንና ትራንስፎርሜሽንን የሚያግዙ ዘመናዊ ኢንስቲቱሽኖች ባለመተከላቸው ሰፊው ህዝባችን ወዴት እንደሚጓዝ ግራ የገባው ይመስላል። ባጭሩ ዛሬ ኢትዮጵያችን በፍጥነት ወደ ማዕከለኛው ዘመን የምትጓዝ አገር ለመሆኗ የአገሪቱ ሁኔታዎች በገሃድ ያረጋግጣሉ። ስለሆነም ዛሬ በመዝናናት ስለ ዕድገትና ትራንፎርሜሽን የምናወራበትና የምንደልቅበት ዘመን ሳይሆን ፣ ሀዘን የምንቀመጥበትና ፣ እየፀለይን እግዚአብሄርን የምንማፀንበት ወቅት ነው። አምላክ ሆይ! ለመሪዎቻችንም ሆነ ለምሁሩ ጥሩ አዕምሮና ቀና ልብ ስጣቸው ብለን እግዚአብሔርን የምንለምንበት ጊዜ ነው። ሌላ ምን ማድረግ ይቻላል ! እስቲ ሌሎች ደግሞ የተሻለ መንገድ አሳዩን። መልካም ንባብ !!

**ፈቃዱ በቀለ**

fekadubekele@gmx.de